Bench book for civil proceedings

መግቢያ ፡-

ይህን ስርዓተ ችሎት (Bench- Book) ለማዘጋጀት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት በዕለት ተዕለት የችሎት አካሄድ ስርዓት ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሁኔታዎችን ዳኛው በቀላሉና በፍጥነት ሊፈታ የሚችልበትን ማጣቀሻ (guideline) ለማዘጋጀት ነው ። ስርዓተ ችሎቱ መደበኛውን የፍ/ሥ/ሥ/ህግ የሚተካ አይደለም ። በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ውስጥ የተካተቱትን ጉዳዬች በሙሉ የያዘም አይደለም ።

የዚህ ስርዓተ - ችሎት ዋና መሠረት የፍ/ሥ/ሥ/ህጉ ሆኖ ነገር ግን ፡-

1. በሥ/ስርዓት ህጉ ውስጥ የተካተቱ ሆነው ነገር ግን ጠቅለል ባለ አገላለጽ የተደነገጉ በመሆናቸው ማብራሪያ የሚሹ ጉዳዬችን ለማብራራት ተሞክሯል ።
2. በህጉ በግልፅ ያልተሸፈኑ ነገር ግን በዕለት ተዕለት የፍ/ቤቶች ሥራ ውስጥ በብዛት የሚያጋጥሙ የሥነ ስርዓት ጉዳዬችን በተመለከተ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ጥረት ተደርጓል ።
3. በስነ - ስርዓት ህጉ የተሸፈኑ ሆነው ነገር ግን በአተረጓጎምና በአተገባበር ረገድ በፍ/ቤቶች ወይም በዳኞች መካከል ልዩነት የሚታይባቸውን ዋና ዋና የስነ ስርዓት ጉዳዬች በተመለከተ በተቻለ መጠን ልዩነቶቹ የሚጠቡበትንና ህጎች በተመሣሣይ ሁኔታ የሚተረጐሙበትንና የሚተገበሩበትን አቅጣጫ ለማሣየት ተሞክሯል ።

ከላይ እንደተገለፀው የስርዓተ- ችሎቱ ዋና መሠረት የሥ/ሥርዓት ህጉ ቢሆንም ማብራሪያ የሚሹ ነጥቦችን ለማብራራትና ክፍተቶችን ለመሙላት ግን ልምድ ያላቸው ዳኞችን ፣ ጠበቆችንና ሌሎች የህግ ሰዎችን በቃልና በጽሁፍ በመጠየቅና በማማከር የተገኙ ሃሣቦች እንዲሁም የሌሎች ሀገሮች ልምድ እንደመነሻ ሃሣብ በጥቅም ላይ ውለዋል።

ስርዓተ- ችሎቱ እንደ ህግ አዛዥነት ባይኖረውም እንዲቀላል ማጣቀሻ ፣ እንደማብራሪያና እንደ ክፍተት መሙያ ግን ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል ።

ክፍል አንድ ፡- የመጀመሪያ ደረጃ መደበኛ የፍትሐብሄር ክርክሮች አካሄድ ንዑስ ክፍል አንድ ፣የመጀመሪያ ደረጃ መደበኛ የፍትሐብሄር ክርክር አጠቃላይ አካሄድ (General outline for first instance ordinary civil proceedings)

1. የክስ አቤቱታ / ከሰነድና ከፅሁፍ ማስረጃ እንዲሁም ከማስረጃ ዝርዝር ጋር / ይቀርባል ።
2. ተከሳሹ የመከላከያ መልሱን ይዞ እንዲቀርብ ይታዘዛል
3. የመከላከያ መልስ / ከሰነድና ከፅሁፍ ማስረጃ እንዲሁም ከማስረጃ ዝርዝር ጋር/ ይቀርባል
4. የመከላከያ መልሱ ከቀረበ በኃላ የጽሁፍ ክርክሩ ያቆማል
5. የጽሁፍ ክርክሩ ካቆመ በኃላ ክሱን ለመስማት ይቀጠራል
6. በተቀጠረው ቀን ባለጉዳዩች ራሣቸው ወይም ወኪሎቻቸው ይቀርባሉ
7. ባለጉዳዩች ከጽሁፍ አቤቱታቸው ጋር ያላቀረቡትን የጽሁፍ ማስረጃ ይዘው ይቀርባሉ
8. የጽሁፍ ማስረጃ ሁሉ በባለጉዳዩች ወይም በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ተጠቃሎ ይገባል
9. ፍርድ ቤቱ ባለጉዳዬችን ወይም ወኪሎቻቸውን ይመረምራል
10. የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከቀረበ ውሣኔ ይሰጥበታል
11. በተደረገው ምርመራ ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ ካመነ ወዲያው ውሣኔ ይሰጣል
12. ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ ካላመነ የክርክሩ ጭብጥ ይያዛል
13. ጭብጡ ከተመሠረተ በኃላ ክርክሩን መስማትና ማስረጃ መመርመር ይቀጥላል
14. ለሁለቱም ወገን ምስክሮች መጥሪያ ይላካል
15. የሁለቱም ወገን ምስክሮች ተሟልተው ይቀርባሉ
16. ከሳሹ / በተወሰኑ ሁኔታዎች ተከሳሹ/ ሙግቱን ይከፍታል
17. ሙግቱን የጀመረው ወገን ምስክሮቹ የሚመሰክሩለትን ነጥብ በአጭሩ ያስረዳል
18. ምስክሮች እውነት ለመናገር ይምላሉ ወይም እውነት እንደሚናገሩ ያረጋግጣሉ
19. ሙግቱን የጀመረው ሰው ምስክሮቹን አንድ በአንድ አቅርቦ ዋና ጥያቄ ይጠይቃል ሌላው ወገን መስቀለኛ ጥያቄ ያቀርባል ። የጀመረው ወገን የማጣሪያ ጥያቄ ይጠይቃል ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ስዓት አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ ይጠይቃል ።
20. ሙግቱን የከፈተው ወገን ምስክሮቹን አሰምት ከጨረሰ በኃላ ሌላኛው ወገን ምስሮቹ የሚያስረዱለትን የመከላከያ ነጥብ በአጭሩ አስረድቶ በተመሣሣይ ሁኔታ ምስክሮቹን ያሰማል ።
21. ማስረጃ የመስማቱ ሂደት ሲጠናቀቅ ግራ ቀኙ የመዝጊያ ቃላቸውን ይሰጣሉ
22. በመጨረሻም ፍርድ ቤቱ በፍርድ ውሣኔውን ይሰጣል ።

ንዑስ ክፍል ሁለት ዝርዝር አካሄድ

1. ክስ ከመሰማቱ በፊት ያሉ ሂደቶች (Pre- trial stages)

1.1 የክስ ማመልከቻን ስለመመርመር

ሀ. ክስ የሚጀመረው የክሱን ምክንያት የሚገልጽ አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ነው (ቁ.213(1))።

ለ. የክስ ማመልከቻ መጀመሪያ የሚቀርበው ለሬጅስትራር ነው ። ሬጅስትራሩ የክስ ማመልከቻው የፍ/ሥ/ሥርዓት ህግ አንቀጽ 80-93 እና 222- 228 በሚያዘው መሠረት ፎርሙን አሟልቶ መቅረቡን ከመረመረ በኃላ በአንቀጽ 229 መሠረት ውድቅ ሊያደርገው ወይም በአንቀጽ 230 መሠረት ሊቀበለው ይችላል ።

ሐ. ሬጅስትራር የክስ ማመልከቻውን ከተቀበለ በቁጥር 214 መሠረት ማመልከቻውን በፍትብሄር ክስ መመዝገቢያ ደብተር ውስጥ ይመዘግባል ።

መ. ሬጅስትራሩ የክስ አቤቱታው በትክክል የቀረበ መሆኑን ተቀብሎ ለችሎቱ ሊያስተላልፍ ፍርድ ቤቱም በተራው በቁጥር 231 መሠረት የክስ ማመልከቻውን ይመረምራል

ሠ. በቁጥር 231(1) (ሀ) ና (ለ) እንዲሁም (2) ሥር በተዘረዘሩት ምክንያቶች ፍርድ ቤቱ ክሱን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል ። የፍርድ ቤቶችን ስልጣን በተመለከተ የፊደራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን በህገ መንግስቱ እና በአዋጅ ቁጥር 25/88 (ከነማሻሻያዎቹ) መሠረት የሚታይ ሲሆን የክልል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ደግሞ በህገ- መንግስቱና በክልሉ ህግ መሠረት ይታያል ።

ረ. በቁጥር 229 ወይም በ231 መሠረት የክስ ማመልከቻው ውድቅ መሆን የሚያስከትለው ውጤት በቁጥር 232 መሠረት ይታያል።

ሰ. ፍርድ ቤቱ በቁጥር 231 መሠረት ክሱን ውድቅ ካላደረገውና ከተቀበለው የክስ ማመልከቻውን / ከማንኛውም አስረጅና የጽሁፍ ግልባጭ ጋር አያይዞ/ ከመጥሪያ ጋር ለተከሳሹ እንዲደርሰውና የመከላከያ መልሱን ጽፎ እንዲያቀርብ ያዛል / ቁ.233/

በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በቀር ቁጥሮች ሁሉ የፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥሮችን የሚመለከቱ ናቸው ።

1.2 ለተከሳሽ መጥሪያ መላክ

ሀ. መጥሪያ ለተከሳሹ የሚላከው ከቁ.94 እስከ 110 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ነው

ለ. የክሱ አቤቱታ ለፍርድ ቤቱ በቀረበ ጊዜ ወዲያው ተከሳሹ ቀርቦ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ያመነ እንደሆነ መጥሪያ መላክ አስፈላጊ አይደለም (ቁ 94 (1))።

ሐ. መጥሪያው ላይ ተከሳሹ በመከላከያ መልሱ ላይ ይጠቀሙኛል ሲል የዘረዘራቸውን ሠነዶች ሁሉ ይዞ እንዲቀርብ መገለጽ አለበት (94(2))።

መ. ተከሳሾች ብዙ በሆኑ ጊዜ የአሰጣጡ ስርዓት በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም ካልተወሰነ በቀር መጥሪያው ለያንዳንዳቸው እንዲደርስ መታዘዝ አለበት (95 (2))።

ሠ. የመጥሪያ አሰጣጥን በተመለከተ ህጉ አማራጮችን በየደረጃቸው አስቀምጧል ። ፍርድ ቤቱ እነዚህን አማራጮች መጠቀም ያለበት ህጉ ባስቀመጠው መሠረት የመጀመሪያና የተከታይ ደረጃዎችን በመከተል መሆን አለበት ። / ለምሣሌ የመጀመሪያውን አማራጭ ተግባራዊ ማድረግ እየተቻለ ሶስተኛውን አማራጭ ማዘዝ የለበትም /

ረ. ከአማራጮቹ የመጀመሪያው የሆነውና በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ ተግባራዊ መሆን ያለበት መጥሪያውን ለተከሳሹ ራሱ መስጠት ነው (ቁ.95(3))።

ሰ. በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ ከቁጥር 96 - 101 ያሉትን አማራጮች በመጠቀም መጥሪያው እንደሁኔታው ለተከሳሹ ነገረ ፈጅ ፣ ለወኪሉ ፣ ለእንደራሴው ወይም ህጉ በሚያዘው መሠረት መጥሪያ ለመቀበል ስልጣን ላለው ሰው እንዲሰጥ ለማዘዝ ይችላል

ሸ. መጥሪያ የተቀበለ ማንኛውም ሰው መጥሪያው የደረሰው መሆኑን ለማረጋገጥ በዋናው መጥሪያ ላይ መፈረም አለበት

ቀ. መጥሪያ የተላከለት ሰው ለመቀበል ፍቃደኛ ያለመሆኑ ወይም ደረሰኝ ለመስጠት እምቢተኝነቱ በመኃላ ቃል የተረጋገጠ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መጥሪያው እንደደረሰው ቆጥሮ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል ለማዘዝ ይችላል (ቁ 103)። አስፈላጊ ሆኖ ከታየው ግን በቁጥር 105 መሠረት ምትክ መጥሪያ እንዲሰጥ ማድረግ ይችላል

በ. ተከሳሹ ወይም ስለሱ መጥሪያ መቀበል የሚገባቸው ሰዎች ተፈልገው ካልተገኙ ወይም ተከሳሹ ወኪል ከሌለው ወይም ተከሳሹ መጥሪያው በደንበኛው ስነ ስርዐት እንዳይደርሰው መሰናክል ካደረገ በቁጥር 105 መሠረት ምትክ መጥሪያ ይሰጣል ።

ተ. ለዋናው መጥሪያ ተጨማሪ የሚሆን ወይም እራሱ ዋናው መጥሪያ ሊሆን የሚችል መጥሪያ በአደራ ፖስታ መላክ ይቻላል (ቁ 106)።

ቸ. በሌላ ፍርድ ቤት ስልጣን ክልል ውስጥ ለሚኖር ተከሳሽ የሚሰጥ መጥሪያ ፣ ከኢትዮጵያ ውጭ ለሚኖር ተከሳሽ የሚላክ መጥሪያና ለመንግስት ወይም ለኩባንያ ሠራተኞች የሚሰጥ መጥሪያ ከቁ.106 — 109 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል።

1.3 <u>የመከላከያ መልስን ስለመመርመር</u>

ሀ. በመጥሪያው መሠረት ተከሳሹ ፍርድ ቤቱ በቀጠረው ቀን የመከላከያ መልሱን ይዞ በቀረበ ፊርድ ቤቱ በአንቀጽ 238 መሠረት መልሱን ይመረምራል ። ስለ ክስ አቤቱታ የተደነገገው ቁጥር 229 የመከላከያ መልስን ለመርመመርም በተመሣሣይነት ተፈፃሚ ይሆናል ።

ለ. የመከለከያ መልሱ ተቀባይነት ካገኘና መከላከያው የከሳሽ ከሳሽነት ክስ ወይም የማቻቻል ጥያቄ ካለው ፍርድ ቤቱ በቁጠር 231 በተደነገገው መሠረት ጥያቄውን መርምሮ መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል (ቁ. 238(2))። ጥያቄው ተቀባይነት ካገኘና ከሳሹ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ከሆነ መልሱን እንዲያቀረብ ፍርድ ቤቱ ያዛል ከሳሹ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መልሱን ባያቀረብ ወይም መልሱ ውድቅ ቢደረግ ዋናውን ክስ በተመለከተ የክስ መስማቱ ሂደት (trial) VnB]sS (ቁ. 239)።

ሐ. የክስ መልሱን ይዞ እንዲመጣ በተቀጠረበት ቀን እራሱም ባይመጣ ወይም መልሱን ይዞ ባይመጣም የክሱ መሰማት ሂደት ይቀጥላል ።

1.4 <u>የጽሁፍ ማሰረጃ ስለሚቀርብበት ጊዜና ሁኔታ</u>

ሀ. የጽሁፍ ማስረጃዎች በሙሉ ክርክሩን መስማትና ምስክሮችን መመርመር ከመጀመሩ በፊት ተጠቃለው መግባት አለባቸው

ለ. በመጀመሪያ ደረጃ ከሳሹ ከክስ ማመልከቻው ጋር ተቀሳሹ ደግሞ ከመከላከያ መልሱ ጋር ይጠቅመናል የሚሉትንና በእጃቸው የሚገኙትን ወይም ሊያቀርቡ የሚችሉትን የጽሁፍ ማስረጃ በሙሉ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው (ቁ. 223(1))። (ለ) እና (1)

ሐ. በሁለተኛ ደረጃ ተከራካሪ ወገኖች ለማቅረብ የሚችሉትንና ይጠቅማናል የሚሉትን ወየም ፍርድ ቤቱ እንዲቀርብ የጠየቀውንና አስቀድመው ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን የጽሁፍ ማስረጃ ሁሉ በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ማቅረብ አለባቸው (ቁ. 137(1))።

መ. ማንኛውም አቤት ባይ ሠነዶችን ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ወይም ከቀነ ቀጠሮው በፊት ወይም በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ካላቀረበ በቀር ማስረጃዬ ከፍርድ ቤቱ መዝገብ ጋር ይያያዝልኝ ወይም ለማቅረብ ይፈቀድልኝ በማለት ለማመልከት አይችልም (ቁ.137 (3))።

ሠ. መቅረብ የሚረባቸው ማስረጃዎች ከተከራካሪዎች ወገኖች ባንዳኛው ጉድለት ወይም በቂ ባልሆነ ምክንያት ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ወዲያው ፍርድ ይሰጣል (ቁ.256 (1))።

ረ. ከላይ በ1 መ" እና "ሠ" ስር የተጠቀሱት አጠቃላይ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ከአቤቱታ ጋር ወይም በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበ የጽሁፍ ማስረጃ በሌላ ጊዜ ሊቀርብ የሚችልበት ልዩ ሁኔታዎች/ (exceptions) አሉ ። እነዚህም

1. ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም በተከራካሪዎች ወገኖች አመልካችነት በሌላ ፍ/ቤት ዘንድ የሚገኝ መዝገብ ወይም የጽሁፍ ማስረጃ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል (ቁ.145 (1))።
2. ማስረጃዎቹ ሳይቀርቡ የቀሩት ከባድና በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳ ስለ ክርክሩ አወሳሰንና ማስረጃ ያለመቅረቡ ስላስከተለው ኪሳራ ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ በመስጠት ነገሩ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ይወስናል (ቁ.256 (1))። ማስረጃው እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላሉ /
3. አስፈላጊ መስሎ ከታየው ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ከመያዙ በፊት በተከራካሪዎች ያልቀረበን የጽሁፍ ማስረጃ በትዕዛዝ አስቀርቦ መመርመር ይችላል(ቁ.149 (1))።
4. ክርክሩ በሚሰማበት በማናቸውም ግዜ ፍርድ ቤቱ በተከራካሪዎቹ ያልቀረበ ነገር ግን ለክርክሩ ጠቃሚ የሆነ የጽሁፍ ማስረጃ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል (ቁ.164)።
5. ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ ለመጠየቅ ወይም ምስክሩ ነገሩን ለማስታወስ እንዲችል የሚቀርብ የጽሁፍ ማስረጃ በመጀመሪያ ባይቀርብም ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ መቅረብ ይችላል (ቁ.137 (4))።

1.5 <u>የጽሁፍ ክርክር የማቀባበል ሥራን ማጠናቀቅ</u>

ሀ. ጽሁፍ የማቀባበል ሥራ የሚጠናቀቀው ከሳሹ ባቀረበው የክስ አቤቱታና የጽሁፍ ማስረጃ ላይ ተከሳሹ የመከላከያ መልሱንና የጽሁፍ ማስረጃውን ሲያቀርብ ነው

ለ. ተከሳሹ ባቀረበው የመከላከያ መልስ ላይ ከሳሹ የመልስ መልስ እንዲሰጥ ሊፈቀድለት አይገባም ።

ሐ. ጽሁፍ የማቀባበሉ ሥራ ከተጠናቀቀ በኃላ በቁ. 241 እና በተከታዮቹ መሠረት ተከራካሪዎቹን መመርመርና የክርክሩን ጭብጥ የመያዝ ሂደት ይቀጥላል ።

2. ክስን ስለመስማት (trial)

2.1 የመጀመሪያ ክርክር ሲከፈት ስለሚፈፀም ስነ ስርዓት

ሀ. መግቢያ

በአጠቃላይ ይህ ደረጃ ወደ ዋናው የክስ መስማት ሂደት መገባት አስፈላጊ መሆን አለመሆኑ የሚለይበት ደረጃ ነው ። የክሱ መስማት የሚቀጥል ከሆነም ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎችን በመመርመር ጉዳዩን የሚረዳበትና ጭብጡን የሚያነጥርበት ደረጃ ነው ።

በዚህ ስርዓት።

በዚህ ስርዓት ፍርድ ቤቱ ክሱ ውስጥ ገብቶ ማከራከሩ / ክሱን በማስረጃ ማጣራቱ / አስፈላጊ ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች ወዲያውኑ አስፈላጊውን ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ ለመስጠት ይችላል ።

ከነዚህም ምክንያቶች ዋንኞቹ፡-

1. ሁለቱም ባለጉዳዩች በመቅረታቸው ወይም ከሳሽ በመቅረቱ መዝገቡ ሲዘጋ ፣
2. ተከሣሹ ቀርቦ ክሱን ሲያምን ወዲያው ውሣኔ ይሰጣል፣
3. ተከራካሪዎችን የሚያከራክር ነጥብ / ጭብጥ/ በሌለ ጊዜ፣
4. በመጀመሪያ መቃወሚያ ክሱ ወይም መዝገቡ ሲዘጋ ፣
5. ከሳሹ በግልግል ወይም በሌላ ምክንያት ክሱን ሲያነሳ ወይም ሲተው / ቁጥር 274፣ 280፣313፣319/ ፣
6. ተከሳሹ የሚፈለግበትን ገንዘብ በሙሉ ሲከፍል (ቁ. 283)።

በነዚህ ምክንያቶች ወይም በሌላ ምክንያት ፍርድ ቤቱ ክሱን ወይም የክሱን መዝገብ ካልዘጋ ወይንም ሌላ የተለየ ትዕዛዝ ካልሰጠ በቁ. 257 እና ተከታዬቹ መሠረት ዋናው የክሱ መሰማት ሂደት ማለትም ክርክሩን መስማትና ምስክሮችን የመመርመር ሂደት ይቀጥላል ።

ለ. ስለተከራካሪ ወገኖች አለመቅረብ

1. ክርክሩን ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ግራ ቀኙ ወገኖች ካልቀረቡ የክስ መዝገቡ ይዘጋል (69(2) ::
2. በቁ. 69 (2) መሠረት የክስ መዝገብ ከተዘጋ ከሳሹ በቁ. 71 መሠረት ተገቢውን ዳኝነት (በድጋሚ) እና ኪሣራ ከፍሎ መዝገቡን ለማስከፈት ይችላል :: ከሳሹ የቀረው በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ ድጋሚ ዳኝነት ወይንም ኪሳራ ላይከፍል ይችላል
3. ከሳሽ ቀርቦ ተከሳሽ ካልቀረበ በቁ. 70 መሠረት እንደ ሁኔታው ተከሳሹ በሌለበት እንዲቀጥል ወይም ሁለተኛ መጥሪያ እንዲላክ ማዘዝ ወይም ክርክሩን ለሌላ ቀጠሮ ማስተላለፍ ይቻላል ::
4. መጥሪያው ለተከሳሹ(ሾቹ) ያልደረሰው በከሳሽ ጥፋት ከሆነ ባልደረሳቸው ተከሳሾች ላይ የክስ መዝገቡ ይዘጋል (70(መ)::
5. በቁ.70 (መ) መሠረት የክስ መዝገቡ ከተዘጋ ከሳሹ የቁ.71ን ሁኔታዎች በማሟላት መዝገቡ እንዲከፈትለት ለመጠየቅ ይችላል :: ቁጥር 74 ለይግባኝ መዝገብ እንጂ ለቀጥታ ክስ ተፈፃሚ አይሆንም :: (በ70(መ) ለተዘጋ መዝገብ ::)
6. በቁ.70(ሀ) መሠረት ተከሳሹ በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ ከታዘዘ በኃላ በሚቀጥለው ቀጠሮ ቀርቦ በመጀመሪያ ቀጠሮ ያልቀረበው በቂ በሆነ እክል መሆኑን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ እንዲከራከር ሊፈቀድለት ይችላል (ቁ.72) ::
7. ተከሳሽ ቀርቦ ከሳሽ ባይቀርብ ፣
   ሀ. ተከሳሹ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ ከሆነ ፍርድ ቤቱ በታመነው መጠን ውሣኔ መስጠት ይችላል (ቁ.73)::
   ለ. ሆኖም ግን ተከሳሽ ስላመነ ብቻ ለከሳሹ የሚወሰን ሳይሆን ተከሳሹ ቢያምንም ከሳሽ ያቀረበው ክስ ህጋዊ መሆኑንና ከሳሹ የጠየቀው ዳኝነት በህግ የሚገባው መሆኑን ፍርድ ቤቱ ማጣራት አለበት ::
   ሐ. ተከሳሹ ክሳደ መዝገቡ ይዘጋል ::
   መ. ሆኖም ከሳሹ በቁጥር 74 በተደነገገው መሠረት የተዘጋው መዝገብ እንዲከፈትለት መጠየቅ ይችላል :: ጥያቄው ተቀባይነት የሚያገኘው ከሳሹ በመጀመሪያው ቀጠሮ የቀረው በቂ በሆነ ችግር መሆኑን ካስረዳ ነው :: ፍርድ ቤቱ ጥያቄውን ከተቀበለ ስለኪሣራውና ስለማናቸውም ወጪ አከፋፈል ተስማሚ መስሎ የታየውን ውሣኔ ከሰጠ በኃላ የተዘጋው መዝገብ እንደገና ተከፍቶ ነገሩ እንዲቀጥል ትዕዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩ የሚሰማበትን ቀጠሮ ይወስናል :: ትዕዛዙ የሚሰጠው የከሳሹ ማመልከቻ ለመልስ ሰጪው ከደረሰው በኃላ ነው :: (በቁጥር 73 መሠረት ለተዘጋ መዝገብ ቁጥር 69 ተፈፃሚ አይሆንም)::

ሐ. ስለ ተከራካሪ ወገኖች መቅረብ

1. ባለጉዳዩ እራሱ መቅረቡ ግዴታ አይደለም ። ስለዚህ ባለጉዳዩ እራሱ መቅረብ ካልፈለገ ወይም ካልቻለ እንደሁኔታው ከቁጥር 57- 64 በተደነገገው መሠረት ነገረ ፈጁ፣ ወኪሉ ወይንም ጠበቃው ቀርቦ መከራከር ይችላል ። እነዚህም በህግ ወይም በውል የተሰጣቸው የውክልና ማስረጃ ሊኖራቸው ይገባል ።
2. ሆኖም ግን ውስን በሆኑና አስፈላጊ በሆኑ ሁኔታዎች ባለጉዳዩ እራሱ እንዲቀርብ ማዘዝ ይቻላል (ቁጥር፣ 68 ና 241(3))።
3. ባለጉዳዩ እራሱ እንዲቀርብ ታዞ በቂ ባልሆነ ምክንያት የቀረ እንደሆነ ወኪሉ ቢቀርብም ስለከሳሽ ወይም ተከሳሽ ያለማቅረብ የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ (ቁጥር77)።
4. ክርክሩን ለመስማት በተቀጠረው ቀን ባለጉዳዩች እራሳቸው ከቀረቡ ማንነታቸው ከተረጋገጠ ወኪሎቻቸው ከቀረቡ ደግሞ ህጋዊ ውክልና እንዳላቸው ከተረጋገጠ በኃላ የክስ መሰማት ሂደት ይቀጥላል (ቁጥር 69(1)እና 241 (1))።

መ. የሶስተኛ ወገኖች ጣልቃ ገብነት ወይም ክስ ውስጥ መግባት

1. ሶስተኛ ወገኖች በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማመልከቻ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ማመልከቻውን ከተቀበለ ከፍርድ ውሣኔ በፊት በክርክሩ ጣልቃ መግባት ይችላሉ (ቁጥር 41)።
2. በተከሳሹ ጠያቂነት ጉዳዩ በእዳነት የሚመለከተው ሌላ ሶስተኛ ወገን በክሱ ውስጥ እንዲገባ ፍርድ ቤት ማዘዝ ይችላል (ቁጥር 43)።
3. አንድ ተከሳሽ በክሱ ውስጥ ያለ ሌላ ተከሳሽ ድርሻውን መክፈል ይገባዋል ብሎ ሲያመለክትም ቁጥር 43 በተመሣሣይ ሁኔታ ተፈፃሚ ይሆናል (ቁጥር 43(4))።
4. በአንቀጽ 43 መሠረት በክሱ ውስጥ እንዲገባ የታዘዘ ሶስተኛ ወገን መጥሪያው ከደረሰው በኃላ ቀርቦ መልስ ሳይሰጥ ወይም ኃላፊ የማይሆንበትን ምክንያት ሳይከራከር የቀረ እንደሆነ ዋናው ተከሳሽ የተፈረደበትን ክስ እንደተቀበለ ተቆጥሮ ከሳሹ ባመለከተው መጠን በኃላፊነት የሚጠየቅበትን ድርሻውን እንዲከፍል ይገደዳል (ቁጥር 76)።

ሠ. ተከራካሪዎቹን ስለመመርመር

1. ባለጉዳዩቹ ሲቀርቡ ፍርድ ቤቱ ስለክርክሩ መነሻ እና ከክርክሩ ጋር አግባቢነት ያላቸውን ጉዳዩች ከባለጉዳዩቹ በመሰለው ዘዴ የቃል ጥያቄ በማቅረብ ይመረምራቸዋል (ቁጥር 241)።
2. ከሳሹ ቀርቦ ተከሳሹ ቢቀርም ይህ ምርመራ በከሳሹ ላይ ብቻ መካሄድ አለበት
3. በዚህ ደረጃ ባለጉዳዩችን በመሰለው የሚመረመረው ፍርድ ቤቱ ነው እንጂ ባለጉዳዩቹ ሙግት አይጀምሩም (ቁጥር 241(2))። የባለጉዳዩች የቃል ሙግት የሚጀመረው በአንቀጽ 258 ነው ። ሆኖም ክሱ በሚከፈትበት ጊዜም ቢሆን ከተከራካሪዎቹ ማንኛውም ወገን እንዲብራራለት የሚፈልገውን ጉዳይ ፍርድ ቤቱ እንዲጠይቅለት ለማመልከት ይችላል (241(2))።
4. ተከሳሹ በመከላከያ መልሱ ወይንም በምርመራው ወቅት በሚሰጠው ቃል የተከሰሰበትን ነገር ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ያመነ እንደሆነ በታመነው መጠን ለከሳሹ ይፈረዳል (ቁጥር 242)። ሆኖም ተከሳሹ ስላመነ ብቻ ለከሳሹ የሚወሰን ሳይሆን ተከሳሹ ቢያምንም ከሳሽ ያቀረበው ክስ ህጋዊ መሆኑንና ከሳሹ ያቀረበው ዳኝነት በህግ የሚገባው መሆኑን ፍርድ ቤቱ ማጣራት አለበት ።
5. ክርክሩ በሚቀጥልበት ሂደት ውስጥ ተከሳሹ ያመነው ጉዳይ ካለም ቁጥር 242 ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል ። በቁጥር 241 የተደነገገው ምርመራም በክርክሩ ሂደት ሁሉ ሊቀጥል ይችላል ቁጥር 243)።
6. ፍርድ ቤቱ ለሚያቀርብለት ጥያቄ ሐሰተኛ ቃል የሰጠን ተከራካሪ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 446 መሠረት ፍርድ ቤቱ ወዲያው በያዘው መዝገብ ላይ ሊቀጣ ይችላል ። ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነም በተመሣሣይ ሁኔታ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁጥር 442 መሠረት መቅጣት ይችላል (484)።
7. ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ከመወሰኑ በፊት ባለጉዳዩን መምከርና በቁጥር 480 መሠረት አስፈላጊ የሆነውን እርምጃ መውሰድ አለበት ። የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው በመጨረሻ ምርጫ መሆን አለበት ።
8. ተከራካሪ ወገኖቹ ወይም አንዱ ችሎቱ የሚካሄድበትን ቋንቋ የማያውቁ ከሆነ ፍርድ ቤቱ አስተርጓሚ መመደብ አለበት ። አስተርጓሚው የመተርጎም ስራውን ከመጀመሩ በፊት የመሐላ ወይም የማረጋጋጫ ቃሉን መስጠት አለበት ። የመኃላ ቃሉም በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ የፎርም ሠንጠረዥ ላይ በተገለፀው መሠረት “ በዚህ ፍርድ ቤት የቀረበውን ክርክር በእውነትና የችሎታዬን ያህል ልተረጉም እምላለሁ “ የሚል መሆን አለበት ።

አስተርጓሚው እምላለሁ ማለትን ኃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ እምላለሁ በማለት ፈንታ አረጋግጣለሁ ማለት ይችላል ። መጽሃፍ ቅዱስ ወይም ቁራን ይዞ እንዲምል ማስገደድ ተገቢ አይደለም ።

9. ክሱ የሚሰማው በግልጽ ችሎት መሆን አለበት ። ሆኖም የተከራካሪዎቹን የግል ህይወት ፣ የህዝብን ሞራልና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ጉዳዩን በዝግ ችሎት ማየት ይቻላል ።

ረ. <u>በመጀመሪያ ደረጃ ክርክር ላይ የሚቀርቡ መቃወሚያዎች</u>

1. ማስረጃ ተቀብሎ ከመመረመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ በፊት ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ላቀረበው መቃወሚያ ውሣኔ መስጠት አለበት (ቁጥር 244(1))።
2. መቃወሚያዎቹ ከአንድ በላይ ከሆኑ ሁሉም አንድ ላይ መቅረብ አለባቸው ። ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያሰናክሉ ካልሆኑ በቀር መጀመሪያ ያልቀረቡ መቃወሚያዎች በኃላ መቅረብ አይችሉም ።(ቁጥር 244(3))።
3. መቃወሚያ መቅረብ ያለበት ከመከላከያ መልስ ጋር ነው እንጂ መጀመሪያ መቃወሚያ ብቻ ቀርቦ ሙሉ መልስ በኃላ የሚቀርብበትን አሠራር ፍርድ ቤቱ መፍቀድ የለበትም ። ስለዚህ ሙሉ መልስ ተሟልቶ ሳይቀርብ መቃወሚያው ብቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት በቁጥር 338 መሠረት የመከላከያ መልሱን ሲመረምር እንዲህ አይነቱን ያልተሟላ መልስ አለመቀበል ወይም ተስተካክሎ እንዲቀርብ ማዘዝ አለበት ።
4. ክሱ ትክክለኛውን ፎርም አልተከተለም የሚል ክርክር እንደመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መቅረብ አይችልም (ቁጥር 24(4))። (ክሱ ፎርሙን መከተሉን የሚያጣራ ሪጅስትራር ስለሆነ ነው)።
5. ፍርድ ቤቱ የቀረበውን መቃወሚያ እንዲሁም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በቁጥር 245 መሠረት ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል ።
6. የቀረበው መቃወሚያ ክሱ የተነሳበት ጉዳይ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ ወይም አስቀድሞ በፍርድ የተወሰነ መሆኑን፣ ወይም በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተፈፀመ መሆኑን፣ ወይም ለዕርቅ የተቀጠረ መሆኑን የሚገልፅ ከሆነና ይህም በማስረጃ ከተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ ክሱን ዘግቶ ባለጉዳዩቹን ያሰናብታል (ቁጥር 245(2))።
7. ከላይ በቁጥር 6 ስር ከተገለፀው ውጪ ያለ መቃወሚያ ሲቀርብና በማስረጃ ሲረጋገጥ ግን ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቶ ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ይሰጣል

8. ከላይ በቁጥር 7 ሥር በተጠቀሰው ሁኔታ መዝገቡ ሲዘጋ ከሳሽ ክሱን አሻሽሎ በዚያው ወይም በሌላ ፍርድ ቤት ክሱን እንደገና ለማቅረብ ይችላል ። ከላይ በቁጥር 7 ሥር በተጠቀሰው ሁኔታ ክሱ ሲዘጋ ግን ከሳሹ በዚያው ጉዳይ ሌላ ክስ ለማቅረብ አይችልም (245(3))።
9. መዝገቡ የተዘጋው ፍርድ ቤቱ በስልጣን በማጣቱ ከሆነ ከሳሹ ካለፈው የዳኝነት ገንዘብ ላይ በደንቡ መሠረት ከሚከፈለው ሂሣብ የቀረው ይመለስለታል (ቁጥር 245(4))።

ለ. የክርክሩን ጭብጥ መያዝ

1. በቁጥር 241 መሠረት ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎቹን በቃል ከመረመረ በኃላ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተነስቶ እንደሆነም በመቃወሚያው ላይ አስፈላጊው ውሣኔ ከተሰጠ በኃላ ባለ ጉዳዩቹ የሚከራከሩበት ወይም የተለያዩበት ጭብጥ ይመሰረታል። (በቀረበው መቃወሚያ መሠረት ክሱ ወይም መዝገቡ ካልተዘጋ በቀር)።
2. ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ወገን ያመነውን ወይም አለ ብሎ የሚከራከረውንና ከክርክሩ ጋር አግባብነት ያለውን የህግ ወይም የፍሬ ነገር ጉዳይ ሌላኛው ወገን ሲክድ ነው (ቁጥር 247(1))።
3. የሚመሠረተው ጭብጥ እንደነገሩ ሁኔታ የህግ ብቻ፣ የፍሬ ነገር ብቻ ወይም የሁለቱም ሊሆን ይችላል
4. በአንድ ክስ ላይ ከአንድ በላይ የሆነ የፍሬ ነገር ወይም የህግ ወይም የሁለቱንም ጭብጦችን መያዝ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል (ቁጥር 247(3) (4)።
5. የህግና የፍሬ ነገር ጭብጦች አንድ ላይ ከተያዙ መጀመሪያ የህግ ጉዳይ ላይ በተያዘው ጭብጥ ላይ ውሣኔ መስጠት አለበት ። ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ፍርድ ቤቱ በህግ ረገድ የተያዙትን ጭብጦች እስኪወሰን ድረስ በፍሬ ነገር የተያዘውን ጭብጥ በቀጠሮ ሊያቆየው ይችላል (ቁጥር 247(4)።
6. የተያዘው ጭብጥ የህግ ጉዳይ ብቻ ከሆነ (የፍሬ ነገር ክርክር ወይም ጭብጥ ከሌለ) ለወዲያው አስፈላጊው ውሣኔ መሰጠት አለበት ።
7. ጭብጥ የሚመሰረተው የግራ ቀኙ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት መሆን አለበት ። ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ከታየው ፍርድ ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ከመመስረቱ በፊት ምስክሮችንና የጽሁፍ ማስረጃዎችን አስቀርቦ መመርመር ይችላል (ቁጥር 249)። በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ መጀመሪያ ተይዘው የነበሩትን ጭብጦች ለማሻሻል ፣ ለመቀየር ወይም ተሳስቶ ተቀብሎ የነበረውን ጭብጥ ለመሠረዝ ይችላል (ቁጥር 251)።

8. በመሰረቱ ጭብጥ የሚይዘው ፍርድ ቤቱ ነው ። ሆኖም ፍርድ ቤቱ ጭብጡን ሲይዝ ጭብጡ ምን እንደሆነ ለባለጉዳዩቹ መግለፅና ሐሳባቸውን መስማት አለበት ።

9. በሌላ በኩልም ተከራካሪ ወገኖች እራሳቸው ጭብጡ ላይ በመስማማት ፍርድ ቤቱ ጭብጡን እንዲይዝላቸው ለማመልከት ይችላሉ (ቁጥር 251)። ፍርድ ቤቱም በቁጥር 253 መሠረት ጥያቄውን መርምሮ ጭብጡን በመቀበል በዚያው መሠረት ውሣኔ ለመስጠት ይችላል ።

10. ክሱ በሚሰማበት ቀን ተከሳሹ የመከላከያ መልሱን ሳያቀርብ ከቀረ ፍርድ ቤቱ የነገሩን ጭብጥ ለመያዝ አይገደድም(ቁጥር 246) (2)። ሆኖም ግን ከሳሹ ካቀረበው ክስ እና የጽሁፍ ማስረጃ እንዲሁም በቁጥር 241 መሠረት በተደረገው የቃል ምርመራ ከተገኘው መረጃ በመነሳት አስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤት መፍትሄ የሚሻውን ጭብጥ ለመያዝ ይችላል ።

11. የክርክሩ ጭብጥ የሚያዘው (ቁጥር 248)።

ሀ. በክሱና በመከላከያው መልስ ውስጥ የተዘረዘሩትን ነገሮች ፣

ለ. ተከራካሪዎቹ ያቀረቡትን የጽሁፍ ማስረጃ፣

ሐ. በቁጥር 241 መሠረት በተደረገው ምርመራ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ (እንደሁኔታው ሶስቱንም ወይም ከሶስቱ ሁለቱን ወይም አንዱን መሠረት በማድረግ)ነው።

12. ከላይ በቁጥር “11” ከተዘረዘሩት ውጪ ሌላ ማስረጃ መቅረቡ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ለመመስረት አስፈላጊ የሆኑ ምስክሮችንና የጽሁፍ ማስረጃዎችን አስቀርቦ መመርመር ይችላል (ቁጥር 249)።

13. ክስ በቀረበበት ሀብት ግምት ላይ ክርክር ከተነሳ ፍርድ ቤቱ ጭብጥ ከመመስረቱ በፊት የሀብቱን ግምት የሚያስታውቁ ምትክ ዳኞችን መሾም አለበት (ቁጥር 250)።

14. ተከራካሪዎቹን የሚያከራክራቸው ነጥብ አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ ከተረዳው ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሳይሆን ወዲያው ተገቢውን ፍርድ መስጠት አለበት (ቁጥር 254)።

15. ተከራካሪዎቹን የሚለያየቸው ነጥብ መኖሩ ከታወቀ ግን ፍርድ ቤቱ ጭብጡን ከመሠረተ በኃላ ተከራካሪዎቹ ወገኖች በመጀመሪያ ክርክር ላይ ያቀረቡት ማስረጃና (በተጨማሪም በቁጥር 249 መሠረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የቀረበው ማስረጃ ክርክር ብቻ ፍትሃዊ ፍርድ ለመስጠት በቂ ከሆነ ወዲያው ፍርድ ይሰጣል (ቁጥር 255)።

16. በመጀመሪያ ክርክር የቀረበው ክርክርና ማስረጃ ብቻ (በ223፣ በ237 እና 256(1) መሠረት በተከራካሪዎቹ የቀረበ ወይም በቁጥር 249 ና 145 መሠረት በፍርድ ቤቱ

ትዕዛዝ የቀረበ ማስረጃ) ጭብጡ ላይ ውሣኔ ለመስጠትና አስፈላጊውን ፍርድ ለመስጠት በቂ ሆኖ ካልተገኘ በቁጥር 257 እና በተከታዬቹ መሠረት ምስክሮችን መመርመር ይቀጥላል ።

2.2 ክርክሩን ስለመስማት እና ምስክሮችን ስለመመርመር

ሀ. መግቢያ

ይህ ደረጃ ዋናው የክስ መስማት ሂደት የሚካሄድበት ነው ። በዚህ ደረጃ የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት ፡-

1. ተከራካሪዎቹ ሙግታቸውን ያሰማሉ ። ምስክሮቻቸውንም አቅረበው ያሰማሉ ።
2. ተከራካሪዎቹ በዋናነት ፍ/ቤቱ ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ምስክሮችን ይመረምራሉ ። ፍ/ቤቱም የምስክሮችን ቃል ይመዘግባል።
3. በቀረበው ክስና ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ፍ/ቤት ፍርድ ይሰጣል ።

ለ. ስለምስክሮች

1. ተከራካሪዎቹ ያቀረቡት የጽሁፍ ወይም የቃል ክርክርና ከአቤቱታዎቻቸው ጋር ወይም በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያቀረቡት የጽሁፍ ማስረጃ እንዲሁም ፍ/ቤቱ ጭብጡን ከመመስረቱ በፊት አስቀርቦ የመረመራቸው የሰውና የጽሁፍ ማስረጃዎች በክርክሩ ላይ ውሣኔ ለመስጠት በቂ ካልሆኑ ፍ/ቤቱ በቁ. 223 መሠረት ተከራካሪዎቹ የዘረዘራቸው ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ያዛል።
2. ሁለቱም ወገኖች የምስክሮች ዝርዝር አቅርበው ከሆነ የሁለቱም ወገን ምስክሮች በአንድ ቀን እንዲቀርቡ መታዘዝ አለበት ።
3. መቅረብ ያለባቸው ተከራካሪዎቹ በአቤቱታቻው ላይ የገለጿቸው ምስክሮች ሁሉ ሳይሆን በጽሁፍ ማስረጃ ያልተረጋገጡና በቁ. 241 መሠረት በተደረገው ምርመራ ተከራካሪዎቹ ያልተማመኑባቸውን የፍሬ ነገር ጭብጥ ለማስረዳት የሚችሉ ምስክሮች ብቻ ናቸው ።
4. አንደኛው ወገን የሌላውን ወገን ምስክር መስቀለኛ ጥያቄ በማቅረብ የመመርመር መብት ስላለው በመሠረቱ ምስክሮች በተቻለ መጠን በአካል ፍ/ቤት ቀርበው ቃላቸውን መስጠት አለባቸው (ቁጥር 261(3))።
5. ከላይ በቁ. 4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በውስን ሁኔታዎች ፍ/ቤቱ ተገቢ መስሎ ሲታየው የፍርድ ቤት እንደራሴ ሆኖ በመወከል ማንኛንም ማስረጃ የሚሰበሰብ ወይም ምስክር የሚመረምር ምትክ ዳኛ መሰየም ይችላል(ቁጥር122- 135)።እንዳሁም ልዩ አዋቂ (ቁጥር 136)።
6. በተጨማሪም ውስን በሆኑ ሁኔታዎች ምስክሩ ፍ/ቤት ሳይቀርብ የመሐላ ቃል እንዲሰጥና ቃሉ በችሎት በንባብ እንዲሰማ ማድረግ ይችላል (ቁጥር 203-206)።

ሐ. ለምስክሮች መጥሪያ መላክ

1. ከላይ በ(ለ) (5) እና (6) ሥር ከተመለከተው ውጪ ምስክር በአካል ፍ/ቤት ቀርቦ መመስከር አለበት ።
2. የመቅረባቸው አስፈላጊነት የታመነባቸው የሁለቱም ወገን ምስክሮች በአንድ ላይ እንዲቀርቡ መጥሪያ ሊደርሳቸው ይገባል ። የመጥሪያው አላላክ ከቁ. 111 እስከ 121 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል ።
3. አመልካቹ ራሱ/ መጥሪያ ሳይጠይቅ / ምስክሮቹን ለማቅረብ ይችላል (ቁጥር 111)።
4. መጥሪያ የሚጠይቀው ወገን መጥሪያውን ከመቀበሉ በፊት ፍ/ቤቱ በወሰነው ልክ ለምስክሮች ማጓጓዣና ሌላ የቀን ወጪ ወይም አበል የሚሆን ገንዘብ እንዲያስቀምጥ ይገደዳል ። ይህን ግዴታ ካልፈፀመ የመጥሪያ ትዕዛዝ ሊሰጠው አይገባም(ቁጥር 212 እና 213)።
5. የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ ወይም የጽሁፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ለሚጠራ ሰው በሚባለው የመጥሪያ ትዕዛዝ ላይ የተጠራበትን ምክንያት ፣ የሚቀርብበትን ቀንና ስዓት ፣ ስፍራው፣ የተጠራው ለምስክርነት ወይም የጽሁፍ ማስረጃ ለማቅረብ ወይም ስለ ሁለቱም ጉዳይ መሆኑ ተለይቶ መገለጽ አለበት (114)።
6. የምስክርነት ቃል ለመስጠት ሳይሆን የጽሁፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብቻ የታዘዘ ሰው ማስረጃው ለፍ/ቤቱ እንዲደርስ ካደረገ ራሱ ለመቅረብ አይገደድም (ቁጥር 115)።
7. ስለተከሳሽ መጥሪያ የተደነገጉት ድንጋጌዎች (ቁጥር 103-105 ከተደነገገው በቀር) ለምስክር በሚሰጥ መጥሪያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ (ቁጥር 116)።
8. መጥሪያው ሲላክ ተጠሪው በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ለመድረስ እንዲችል ለመጓጓዣና አስፈላጊውን መሰናዳት ለማድረግ በቂ ሆኖ በሚገመት ጊዜ ውስጥ ሊደርሰው እንዲችል መደረግ አለበት
9. መጥሪያው የተላከለት ሰው መጥሪያው ስላልደረሰው ሳይቀርብ የቀረ ወይም የጽሁፍ ማስረጃውን ሳያቀረብ ከቀረና ምስክሩ ወይም የጽሁፍ ማስረጃው መቅረቡ ጠቃሚ ከሆነ ባለ ጉባዩ ተገቢውን ኪሣራ ከፍሎ ሌላ መጥሪያ እንዲደርሰው ይታዘዝለታል (ቁጥር 118(2) (ሀ)።
10. የተጠራው ሰው መጥሪያው ደርሶት ሳይቀርብ የቀረው በቂ ባልሆነ ምክንያት ከሆነ ወይም እንዳይደርሰው ሆነ ብሎ ከተሰወረ ተጠሪው ተገዶ ወይም ታስሮ እንዲቀረብ ፍ/ቤቱ ያዛል

(ቁጥር 118(2)(ለ))። በተጨማሪም በወ/መ/ህ/ቁ 442 መሠረት በወንጀል ሊቀጣው ይችላል (ቁጥር 118(3) እና 481)።

11. ክርክሩን ለመስማት በተቀጠረው ቀን የሁለቱም ወገን ምስክሮች በአንድ ላይ ተሟልተው መቅረብ አለባቸው ።

መ. **የምስክሮች ተሟልተው አለመቅረብ**

1. ከሁለቱም ወገን ምንም ምስክር ካልቀረበ ወይም ምስክሮች በከፊል ብቻ ከቀረቡ / መጥሪያውን እንዲያደርስ የታዘዘው ቁ. 95 (1) በሚያዘው መሠረት መጥሪያ ሰጪ ሳይሆን ባለጉዳዩቹ ራሳቸው እንዲያደርሱ በታዘዙ ጊዜና ክርዝሩን የመጀመርና ማስረጃ በቅድሚያ የማሰማት መብት የከሳሹ በሆነበት ሁኔታ)፡-

የሁለቱም ወገን ምስክሮች ካልቀረቡ

ሀ. በሁለቱም ባለጉዳዮች ጥፋት ከሆነ መዝገቡ ላይ ባለው ማስረጃ አስፈላጊውን ውሣኔ መስጠት ወይም ክሱን መዝጋት እንጂ ምስክሮቹ እንዳቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መሰጠት የለበትም (ቁጥር 196 እና 199)

ለ. የከሳሽ የቀሩት በከሳሹ ጥፋት ሆኖ የተከሳሹ የቀሩት ግን በጥፋቱ ሳይሆን ከዓቅም በላይ በሆነ ችግር ከሆነ የከሳሹን ምስክር ለመስማት ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም ። ክሱን መዝጋት ወይም አስፈላጊውን ውሣኔ መስጠት ወይም የከሳሹ ምስክሮች ባይሰሙም በተከሳሽ ምስክር መጣራት ያለባቸው ነጥቦች ካሉ የተከሳሽ ምስክሮችን ብቻ ሰምቶ አስፈላጊውን ውሣኔ መስጠት ።

ሐ. የከሳሹ የቀሩት ከዓቅም በላይ በሆነ ችግር የተከሳሹ የቀሩት በተከሳሹ ጥፋት ከሆነ የከሳሹን ምስክሮች ብቻ ሰምቶ አስፈላጊውን ትዕዛዝ ወይም ውሣኔ መስጠት ። የተከሳሹ ምስክሮች እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም ።

የከሳሽ ምስክር ምንም ሳይቀርቡ የተከሳሽ የተወሰነ ወይም በሙሉ ቢቀርቡ ፣

ሀ. የከሳሽ ምስክር ያልቀረቡት ከዓቅሙ በላይ በሆነ ችግር ከሆነ ምስክሮቹ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መስጠትና እንዲሁም የተከሳሹን ምስክሮች መመለስና በሚቀጥለው ቀነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ ማዘዝ ። በተከሳሹና በምስክሮቹ ላይ ለደረሰው መጉላላት በቂ ኪሣራ መወሰን ።

ለ. በከሳሹ ጥፋት ከሆነ ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም ። ክሱን መዝጋት ወይም አስፈላጊውን ውሣኔ መስጠት ። የከሳሹ ምስክር ባይሰሙም በተከሳሽ ምስክር መጣራት ያለባቸው ነጥቦች ካሉ የተከሳሽ ምስክሮችን ብቻ ሰምቶ አስፈላጊውን ውሣኔ መስጠት ።

የከሳሽ የተወሰኑ ብቻ ቀርበው የተከሳሽ በሙሉ ወይም በከፊል ቢቀርቡ

ሀ. ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ከሆነ የቀረቡትን የከሳሽ ምስክር መስማት ያልቀረቡት መቅረባቸው የግድ አስፈላጊ ከሆነ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መስጠት ። የተከሳሽ ምስክሮች እንዲመለሱና በሚቀጥለው ቀነ - ቀጠሮ እንዲቀርቡ ማዘዝ ። በተከሳሽና በከሣሹ ምስክሮች ላይ ለደረሰው መጉላላት ተገቢውን ኪሣራ መወሰን ።

ለ. በከሳሹ ጥፋት ከሆነ የቀረቡትን ምስክሮች ብቻ መስማት ። የቀሩት እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም ። የተሰሙት የከሳሽ ምስክሮች ብቻ እንደክሱ ካላስረዱ ክሱን መዝጋት ወይም አስፈላጊውን ውሣኔ መስጠት ። የተሰሙት ብቻ ክሱን በማስረዳታቸው ወይም ባያስረዱም አንዳንድ ነጥቦችን ለማጣራት የተከሳሽን ምስክር መስማት አስፈላጊ ከሆነ መስማት ።

<u>የከሳሽ በሙሉ ቀርበው የተከሳሽ ምንም ካልቀረበ :-</u>

ሀ. በተከሳሽ ጥፋት ከሆነ የከሳሽ ብቻ ተሰምተው አስፈላጊው ውሣኔ ይሰጣል የተከሳሹን ምስክር ለመስማት ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም

ለ. በተከሳሹ ጥፋት ሳይሆን ከዓቅም በላይ በሆነ ችግር ከሆነ የከሳሹን ሰምቶ የተከሳሹ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መስጠት ። በከሳሹ ላይ ለደረሰው መጉላላት ተገቢውን ኪሣራ ተከሳሽ እንዲከፍል ማዘዝ

<u>የከሳሽ በሙሉ ቀርበው የተከሳሽ በከፊል ብቻ ቢቀርቡ</u>

ሀ. በተከሳሹ ጥፋት ከሆነ የከሳሽ ከተሰሙ በኃላ እንደ ክሱ ካስረዱ የቀረቡትን የተከሳሽ ምስክር ብቻ መስማት ። የቀሩት እንዲቀርቡ ሌላ ቀነ ቀጠሮ አይሰጥም።

ለ. ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ወይም ምክንያት ከሆነ የከሳሽ ምስክሮች ከተሰሙ በኃላ እንደ ክሱ አስረድተው ከሆነ የቀረቡትን የተከሳሽ ምስክሮች መስማት ። የቀሩት የተከሳሽ ምስክሮች መቅረብ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መሆናቸው ከታመነበት የቀረቡትን ሰምቶ የቀሩት እንዲቀርቡ ሌላ ቀነ ቀጠሮ መስጠት ። ቀጠሮ ከተሰጠ በከሳሹ ላይ ለደረሰው መጉላላት ተከሳሽ በቂ የሆነ ኪሣራ እንዲከፍል ማዘዝ ።

2. ከላይ በቁ.1 የተመለከተው ሁኔታ ፍ/ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ የግድ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ያልቀረበው ምስክር እንደተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀረብ ከማዘዝ አያግደውም ።
3. ምስክሩ የቀረው በባለጉዳዮች ጥፋት ሳይሆን መጥሪያ በትክክል ከደረሰው በኃላ በእምቢተኝነት የቀረ እንደሆነ በቁ. 118/2/ /ለ/ የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል ።
4. ምስክሮች ተሟልተው ከቀረቡ ወይም በከፊል ቢቀርቡም የቀረቡት እንዲሰሙ ፍ/ቤት የወሰነ እንደሆነ ምስክሮችን መመርመር ይቀጥላል ።

5. የቀረቡትን ምስክሮች በአንድ ቀን ሰምቶ መጨረስ ካልቻለ ፍ/ቤቱ ምስክሮቹን ሁሉ ሰምቶ እስኪጨርስ ድረስ በየዕለቱ አዳሪ የሚሆን ቀጠሮ እየሰጠ ስራውን ማከናወን አለበት እንጂ ረጅም ቀጠሮ መስጠት የለበትም (ቁጥር 197(3)።

ሠ. የተከራካሪዎቹ ሙግት መጀመርና ምስክሮችን መመርመር

1. ስለ ክሱ መከፈትና ሙግትን የመጀመር መብት

1.1 ክስን መክፈትና ሙግትን የመጀመር መብት የከሳሽ ነው ። ነገር ግን ተከሳሹ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ አምኖ ነገር ግን ህግ ወይም ሌላ ፍሬ ነገር በመጥቀስ የቀረበብኝ ክስ ዋጋ የለውም ብሎ የሚከራከር ከሆነ ሙግቱን የሚጀምረው ተከሳሹ ይሆናል (ቁጥር 258(1)።

1.2 ክሱን የሚጀመረው ወገን የመክፈቻ ቃሉን ከሰጠና ምስክሮቹ የሚመሰክሩለትን ነጥብ በአጭሩ ካስረዳ በኃላ የሚደግፈውን ማስረጃ አቅርቦ ያሰማል (ቁጥር 259(1)።

1.3 ክሱን የሚጀምረው ወገን ማስረጃውን አሰምቶ ከጨረሰ በኃላ ሌላኛው ወገን የራሱን የመከላከያ መክፈቻ ቃል ካሰማና የመከላከያ ምስክሮቹ የሚመሰክሩለትን ነጥብ በአጭሩ ካስረዳ በኃላ የመከላከያ ምስክሩን አቅርቦ ያሰማል (ቁጥር 259(2)።

2. የማስረጃ አቀራረብ

2.1 ምስክር የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት የመኃላ ቃል ወይም የሚሰጠው ቃል እውነተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቃል መስጠት አለበት (ቁጥር 261(1)።

2.2 የሚሰጠው የመኃላ ቃል በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ የፎርም ሠንጠረዥ ላይ በተገለፀው መሠረት " በዚህ ፍርድ ቤት ፊት የምሰጠው ቃል እውነት ፣ በሙሉ እውነት ፣ እውነት እንጂ ሌላ ምንም እንደማይሆን እምላለሁ ። የሚል መሆን አለበት ። ምስክሩ " እምላለሁ " ማለትን ኃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ " እምላለሁ" በማለት ፈንታ " አረጋግጣለሁ " ማለቱ በቂ ነው "" ምስክሩ መጽሃፍ ቅዱስ ወይም ቁራን ይዞ እንዲምል ማስገደድ አስፈላጊ አይደለም።

2.3 ስለራሱ ጉዳይ የምስክርነት ቃል መስጠት የሚፈልግ ተከራካሪ ወገን መመስከር ይችላል የሚመሰክረውም እውነት እንደሚናገር ከማለ ወይም ካረጋገጠ በኃላ መሆን አለበት ።

2.4 ምስክሩን ያቀረበው ወገን ለራሱ ምስክሮች ዋና ጥያቄ (wxamination- in- chief) በማቅረብ ይመረምራቸዋል ። በዋና ጥያቄ ወቅት መሪ ጥያቄ አይፈቅድም ። ሆኖም ፍ/ቤቱን በማስፈቀድ መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል (ቁጥር 263(1) (2)።

2.5 በዋና ጥያቄ ጊዜ የሚቀርበው ጥያቄ ጭብጡን የሚመለከትና ምስክሩ በቀጥታ ወይም በሌላ መንገድ በሚያውቀው ወይም ሊያውቀው በሚችለው ነገር ላይ ብቻ ነው (ቁጥር 263(1)።

2.6 ምስክሩን ያቀረበው ወገን ዋና ጥያቄ አቅርቦ ከጨረሰ በኃላ ተቃራኒው ወገን መስቀልኛ ጥያቄ በማቅረብ ምስክሩን ይመረምረዋል ። በመስቀልኛ የሚቀርበው ጥያቄ ምስክሩ በዋና ጥያቄ የሰጠው የምስክርነት ቃል የተሳሳተበትን ፣ ሀሰት ነው የሚባልበትን ወይም አጠራጣሪ መስሎ የተገመተበትን ነጥብ ፍ/ቤቱ እንዲረዳ ለማድረግ የሚቀርብ ነው ። ስለዚህ በመስቀለኛ ጥያቄ ወቅት በዋና ጥያቄ ላይ ከተነሳው ነጥብ ጋር የማይገናኝ ወይም ወደዚያ የማያመራ አዲስ ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም ። ሆኖም በመስቀለኛ ጥያቄ ወቅት ምስክሩን መምራት ይቻላል (ቁጥር 263(3)።

2.7 የመስቀለኛ ጥያቄ ካለቀ በኃላ የመጀመሪያው ጠያቂ የማጣሪያ ጥያቄ ያቀርባል ። በማጣሪያ ጥያቄ ወቅት በመስቀልኛ ጥያቄ ላይ ከተነሳው ነጥብ ጋር የማይገናኝ ወይም ወደዚያ የማያመራ አዲስ ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም ። ጥያቄው የሚጠየቀው ምስክሩ በመስቀልኛ ጥያቄ ወቅት የሰጠውን ቃል ለማብራራት ብቻ ነው (ቁጥር 263(4)።

2.8 ምስክርን የመመርመር ሥራ በዋናነት የባለጉዳዩቹ ቢሆንም ስለ ጉዳዩ መብራራትና ስለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ መስሎ የታየው እንደሆነ ፍ/ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ምስክሩን ለመጠየቅ ይችላል (ቁጥር 261(4)።

2.9 በጥያቄ አቀራረብ ላይ መቃወሚያ ሲነሳ ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን ሳይቀበል ለጥየቄው መልስ እንዲሰጥበት ያዘዘ እንደሆነ መቃወሚያው የቀረበበትን ጥያቄ ፣ የተሰጠውን መልስ ፣ የተቃወመውን ሰው ስም ፣ መቃወሚያው ውድቅ የሆነበት ውሣኔ በመዝገቡ ላይ ማሰፈር አለበት(ቁጥር 270)።

2.10 አንድ ባለጉዳይ ያቀረበው ምስክር መልሶ በባለጉዳዩ ላይ ቢመስክር ባለጉዳዩ ይህ ቃል እንዳይመዘገብ ምስክሩም ቃሉን መስጠት እንዲያቆም ፍ/ቤቱን መጠየቅ አይችልም ። ጥያቄው ቢቀርብም ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ሳይቀበል የምስክሩን ቃል መመዝገብ አለበት ። ባለጉዳዩ ጥያቄውን ቢያቆም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሩን መመርመር መቀጠል ይችላል ።

2.11 የምስክሩ ቃል የተሰጠው በችሎቱ ቋንቋ ሳይሆን በሌላ ከሆነ አስተርጓሚ ይመደባል። አስተርጓሚውም የመተርጎም ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የመኃላ ቃል ወይም በትክክል እንደሚተረጉም የሚያረጋግጥ ቃሉን መስጠት አለበት ። የመኃላ ቃሉም በፍ/ሥ/ሥ/ህጉ የፎርም ሠንጠረዥ ላይ በተገለፀው መሠረት " በዚህ ፍ/ቤት

የሚሰጠኝን ማስረጃ በእውነትና የችሎታዬን ያህል ልተረጉም እምላለሁ ። የሚል መሆን አለበት ።አስተርጓሚው " እመላለሁ " ማለትን ኃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ " እምላለሁ " በማለት ፈንታ " አረጋግጣለሁ " ማለት ይችላል ። መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ቁራን ይዞ እንዲምል ማስገደድ ተገቢ አይደለም።

2.12 የተሰጠው የምስክርነት ቃል በቁ. 269 የተደነገገውን ፎርምና ይዘት ተከትሎ መመዝገብ አለበት ።

3. <u>የፍ/ቤቱ ስልጣን</u>

3.1 ምስክሮችን አቅርቦ ማሰማት በዋናነት የባለጉዳዩቹ ቢሆንም ለክርክሩ ጠቃሚ መስሎ ከታየው ተከራካሪዎቹ ካቀረቡት ምስክር በቀር ተጨማሪ ምስክር ጠርቶ መስማት ይችላል(ቁጥር 264)። ሆኖም ፍ/ቤቱ ተጨማሪ ምስክር መስማት ያለበት ለፍትህ አሰጣጥ የግድ አስፈላጊ ሲሆንና በውስን ሁኔታዎች ብቻ እንዲሁም ገለልተኝነቱን በማይነካ መልኩ መሆን አለበት ።

3.2 ለፍትህ አሰጣጥ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ክርክሩ በማናቸውም ደረጃ በሚገኝበት ጊዜ ቀድሞ መስክረው የነበሩትን ምስክሮች ፍ/ቤቱ እንደገና አስጠርቶ ማናቸውንም ተገቢ መስሎ የታየውን ጥያቄ ሊጠይቃቸው ይችላል (ቁጥር 266)።

3.3 በቁ. 265 የተገለፀው ሁኔታ ሲያጋጥም ፍ/ቤቱ የምስክሩን ቃል ባስቸኳይ መቀበል ይችላል ።

3.4 ክርክሩ በማናቸውም ደረጃ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ ፍ/ቤቱ ክርክር የተነሳበት ማናቸውንም ንብረት ወይም ማናቸውንም ነገር ስፍራው ድረስ ሄዶ በማየት ለመመርመር ይችላል (ቁጥር 272)።

4. <u>የምስክር ቃልን ለመስጠት ፈቃደኛ ስላለመሆንና ሐሰተኛ የምስክርነት ቃል</u>

4.1 ማንኛውም በፍ/ቤት ችሎት የቀረበ ተከራካሪ ወገን ወይም ሌላ ሰው የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ወይም በእጅ የሚገኘውን ወይም በስልጣኑ ሥር የሚገኘውን የጽሁፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍ/ቤቱ ሲያዘው በቂ ባልሆነ ወይም በህግ በማይደገፍ ምክንያት ትዕዛዙን ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ወዲያውኑ ይፈረድበታል ። ወይም ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢ መስሎ የታየውን ሌላ ትዕዛዝ ይሰጣል ።

4.2 በዚህም መሠረት ፍ/ቤቱ በቁ. 480 በተጠቀሰው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላላል

4.3 በተጨማሪም እምቢተኛውን በወ/መ/ህ/ቁ. 442 መሠረት ወዲያው መቅጣት ይችላል (ቁጥር 481)። ሆኖም ይህን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ምስክሩ ቃሉን ለመስጠት ያልፈለገበትን ምክንያት (ለምሣሌ ጥያቄውን ቢመልስ የወንጀል ክስ ሊያስከትልብኝ ይችላል ብሎ በመፍራት እንደሆነ) ማጣራትና ምስክሩ ቃሉን መስጠቱ አስፈላጊ መሆኑን፣ ቃሉን መስጠቱም ግዴታው መሆኑን፣ በእምቢተኝነቱ ከቀጠለ ግን የወንጀል ቅጣት ሊወሰንበት እንደሚችል ማስረዳትና አስፈላጊውን ምክር ሁሉ መስጠት አለበት ። ፍ/ቤቱ አስፈላጊውን ማጣሪያ ካደረገና ተገቢውን ምክር ከሰጠ በኃላ ምስክሩ በእምቢተኝነቱ ከቀጠለና ሌላ አማራጭ የሌለ መስሎ ከታየው የወንጀል ቅጣቱን መወሰን ይችላል።

4.4 ምስክሩ ሐሳቡን ቀይሮ የምስክርነት ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኝነቱን ከገለፀና ቃሉን ከሰጠ ፍ/ቤቱ የወሰነበትን ቅጣት ሊያቀልለት ወይም ቅጣቱን ሙሉ በሙሉ አንስቶለት በተግሳፅ ብቻ ሊያልፈው ይችላል ።

4.5 ምስክሩ ግልጽ የሆነ የሐሰተኛ ምስክርነት ቃል ከሰጠ ቃሉን ያስተካክል እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተገቢውን ጥረት ካደረገና አስፈላጊውን ምክር ከሰጠው እንዲሁም በሀሰት መመስከር ወዲያው በወንጀል እንደሚያስቀጣው ካስረዳው በኃላ ምስክሩ በእምቢተኝነቱ ከቀጠለ በወ/መ/ሕ/ቁ. 447 መሠረት ምስክሩን ወዲያው መቅጣት ይችላል (ቁጥር 481)።

4.6 ከላይ በቁ(ቁጥር 4.5) በተገለፀው መሠረት ቅጣት የተወሰነበት ምስክር በራሱ ፈቃድ ቃሉን ወዲያው በማስቀረት በተግሳፅ ብቻ ሊያልፈው ይችላል (ቁጥር 481)።

4.7 የሀሰት ቃል የሰጠው ተከራካሪ ወገን ከሆነ በወ/መ/ሕ/ቁ. 446 መሠረት ወዲያው ቅጣት ሊበይንበት ይችላል ። በዚህም ጊዜ ከላይ በቁ.(4.5) እና (4.6) የተመለከቱት ሁኔታዎች እና ጥንቃቄዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ መሆን አለባቸው ።

3. ፍርድ

3.1 የማስረጃ መስማት ስርዓት ተጣርቶ ካለቀ በኃላ ተከራካሪ ወገኖች የመዝጊያ (የማጠቃለያ) ቃላቸውን ይሰጣሉ ። ሙግቱን የጀመረው ወገን መጀመሪያ ስለ ክርክሩ አጠቃላይ የመዝጊያ ቃሉን ይሰጣል ። ከዚያ ሌላኛው ወገን ስለ ክረክሩ ያለውን አስተያየት በመዝጊያ ቃል ያቀርባል ። በመጨረሻም ክርክሩን የጀመረው ወገን ለክርክሩ ያለውን ጠቅላላ የመዝጊያ ሐሳብ ያቀርባል (ቁጥር 258 እና 273)።

3.2 የማስረጃ መሰማት ስርዓቱ ተጣርቶ ካለቀና ከላይ የተጠቀሰው የመዝጊያ ቃል ከተሰጠ በኃላ ፍ/ቤቱ የፍርድ ውሣኔ ይሰጣል (ቁጥር 273)።

3.3 ለፍርድ ውሣኔው መሠረት ሊሆኑ የሚችሉት ማስረጃዎች

1. የምስክሮች ቃል(ባለጉዳዩቹ አቅራቢነት ወይም በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ቀርበው ቃላቸውን የሰጡ ፣ በምትክ ዳኛ የተሰበሰቡ የምስክሮች ቃል ወይም ከፍ/ቤቱ ውጪ በመኃላ የተሰጡ የምስክሮች ቃል)
2. በኤክስፐርቶች የተሰጡ ማረጋጋጫዎች፣
3. በባለጉዳዩቹ ወይም በፍ/ቤት ትዕዛዝ የቀረቡ የጽሁፍ ማስረጃዎችና ሠነዶች፣
4. በምትክ ዳኛ የተሰበሰቡ ሌሎች ማስረጃዎች
5. ባለጉዳዩቹ በጽሁፍ ወይም ፍርድ ቤቱ በሚመረምራቸው ጊዜ የሚሰጧቸው የእምነት ቃላት ፣
6. ፍ/ቤቱ በቁ. 272 መሠረት ባደረገው ምርመራ የተገኙ መረጃዎች ፣
7. የታወቁ ጉዳዬች (legal presumption)
8. በህግ የተወሰደ የህሊና ግምት (legal presumption)
9. ያንዱን ነገር አፈጣጠርና ሂደት ማሳያ (demonstration)
10. ፍ/ቤቱ በዓይነት እንዲመለከታቸው የሚቀርቡለት ነገሮች (exhibits)

3.4 የእነዚህን ማስረጃዎች ተቀባይነት (admissibility) እና እውነተኛነት(credibility) ፍ/ቤቱ ይወስናል ።

3.5 ባለጉዳዩቹ ወይም ወኪሎቻቸው የመክፈቻና የመዝጊያ ንግግር ሲያደርጉ ወይም ምስክሮችን በሚመረምሩበት ጊዜ የሚኖሯቸው ቃላት እንደማስረጃ መወሰድ የለባቸውም።

3.6 ከላይ በክፍል /ሠ/ /3/ ከተጠቀሰው ውጪ ዳኛው ከችሎት ውጭ ያያቸው ወይም የሰማቸው ነገሮች ወይም ያገኛቸው ማስረጃዎች ለውሣኔው መሠረት መሆን የለባቸውም ።

3.7 የቀረበው ክርክር ከተሰማ በኃላ ፍ/ቤቱ ነገሩ እንደላቀ ወዲያውኑ ወየም በአጭር ቀነ ቀጠሮ በሚወሰነው ጊዜ በግልጽ ችሎት ፍርድ መስጠት አለበት (ቁ. 180)።

3.8 የፍርድ አሰጣጥ፣ የውሣኔው አፃፃፍና ፎርም በቁ. 181 እና 183 በተደነገገው መሠረት መሆን አለበት ።

3.9 በአንድ የፍርድ ሐተታ ላይ የተያዘው ጭብጥ ፣ ጭብጡ እንዴት እንደተወሰነና የተወሰነበት ምክንያት መገለጽ አለበት ። በመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጥ ፍርድ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ዋነኛ ጉዳይ ባጭር የሚገልጽ መሆን አለበት (ቁ. 182(1))

3.10 የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ተከራካሪዎቹ ወገኖች በዝርዝር ባላቀረቡት ወይም በግልጽ ባላመለከቱት ጉዳይ ላይ ፍርድ ለመስጠት አይችልም (ቁ. 182(2))

3.11 በክርክሩ ላይ ከቀረቡት ብዙ ጭብጦች አንዱ ጭብጥ ብቻ ቢወሰን ሌሎቹንም ጭብጦች የሚያጠቃልል ከሆነ ክርክሩ ባንዱ ጭብጥ ብቻ ሊወሰን ይችላል ። ካልሆነ ግን እያንዳንዱ ጭብጥ ለየብቻው ውሣኔ ማግኘት አለበት (ቁ. 182(4))

ክፍል ሁለት ፡- ልዩ ስነ- ስርዓት

1. መግቢያ

በክፍል አንድ የተመለከተው መደበኛ የክርክር ሂደት የተከሳሹ የመሰማት መብት (The right to be heard) የሚከበርበትና ረጅምና ውስብስብ ሂደት የሚካሄድበት የክርክር ሂደት ነው ፡፡

በዚህ ክፍል የተመለከቱት ስርዓቶች ግን የተከሳሹ የመሰማት መብት የተገደበበት ወይም የሌለበት፣ አጭርና በተፋጠነ ሁኔታ እንዲሁም ውስብስብ ባልሆነና ቀላል በሆነ አካሄድ ክርክሮች የሚካሄድበትና ውሣኔ የሚሰጥበት ነው ፡፡

እነዚህ ስርዓቶች የተከሳሹ የመሰማት መብት ከመጠበቅ ይልቅ የተቀላጠፈ ፍትህ ማግኘቱ የበለጠ ሚዛን ይደፋል ተብሎ የሚታመንባቸውን ጉዳዬች የሚመለከቱ ናቸው ፡፡ ጉዳዬቹ በመደበኛው ስርዓት ሳይሆን በልዩ ስርዓት እንዲታዩ የተደነገገውም ጉዳዩቹን ለመወሰን የሚፈጀው ጊዜና ወጪ ከጉዳዩ ባህሪ ጋር እንዲመጣጠን ለማስቻል ታስቦ ነው ፡፡

ስለዚህ በዚህ ክፍል በተገለፀው መሠረት በልዩ ስርዓት መታየት የሚገባቸውን ጉዳዩች ፍ/ቤቱ በመደበኛው ስርዓት ሳይሆን አግባብ ባለው ልዩ ስርዓት ማስተናገድ አለበት

2. በአጭር ሁኔታ ስለሚወሰኑ ክርክሮች (summary procedures)

2.1 ከቁ. 284 እስከ 292 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል

2.2 በዚህ ስርዓት መሠረት ክስ ሊቀርብ የሚችለው በቁ. 284 ሥር በተዘረዘሩ ጉዳዩች ብቻ ነው ::

2.3 ማመልከቻው በመኃላ ቃል ተደግፎ መቅረብ አለበት (284 (ሐ))። የመኃላ ቃሉ ተከሳሹ ለነገሩ ምንም ዓይነት መከላከያ እንደሌለው ከሳሽ የሚያምን መሆኑን መግለጽ አለበት ::

2.4 ፍ/ቤቱ ማመልከቻውን ከተቀበለ በኃላ ለተከሳሹ መጥሪያ እንዲደርሰው ያዛል (ቁ.(285 (1))።

2.5 ተከሳሹ ቀርቦ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ፍ/ቤቱን ጠይቆ ካላስፈቀደ በቀር መከላከያ ሊያቀርብ አይችልም (285 (1))።

2.6 ተከሳሹ ቀርቦ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ለፍ/ቤቱ ካላመለከተ ወዲያው ፍርድ ይሰጣል (285 (2))።

2.7 ለመከላከል ፈቃድ እንዲሰጥ የሚቀርበው ማመልከቻ በቁ. 286 መሠረት በመኃላ ቃል ተደግፎ መቅረብ አለበት ::

2.8 ተከሳሹ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካጣ ወዲያው ለከሳሹ ይፈረዳል (287)) ::

2.9 ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ ግን ተከሳሹ መከላከያ እንዲያቀርብ ይፈቀድለታል :: ክሩክሩም የሚመራው ፍ/ቤቱ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ወይም እንደመደበኛው ክስ በቀጥታ ሊሆን ይችላል (ቁ. 290 እና 291) ::

2.10 ፍርድ ከተሰጠ በኃላ ለተከሳሹ የተላከው መጥሪያ በአግባቡ ያልደረሰው ከሆነ ፍ/ቤቱ ፍርዱ ከመፈፀም እንዲቆይ በማድረግ ተከሳሹ ቀርቦ እንዲከላከልና ስለ ጉዳዩም አፈፃፀም ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ለመስጠት ይችላል (ቁ. 292)

3. የተፋጠነ ስነ ስርዓት (Accelerated procedure)

3.1 ከቁ. 300 እስከ 314 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል

3.2 በመሠረቱ ይህ ስርዓት የሚፈቀደው በቁ.305 እና 307 እና 307-314 በተዘረዘሩት ጉዳዩች ነው (ቁ. 300)11) ።

3.3 ሆኖም ግን ጉዳዩ በዚህ ስርዓት መታየት የለበትም ብሎ ፍ/ቤቱ መከልከል የሚችል ሆኖ ከላይ በተጠቀሱት ቁጥሮች ከተደነገጉት ጉዳዩች ውጪም ቢሆኑ ሌሎች ጉዳዩች በዚህ ስርዓት መታየት ይችላሉ (ቁ. 300)11) ።

3.4 ማመልከቻው የሚቀርበው በቁ. 301 የተደነገገውን ሁኔታ አሟልቶና በመኃላ ቃል ተደግፎ መሆን አለበት ።

3.5 ማመልከቻው በቁ. 302 ስር በተዘረዘሩት ምክንያቶች ውድቅ ሊሆን ይችላል ።

3.6 ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሚሰጠው በማመልከቻው ላይ በተገለፀው እና አምልካቹ ከማመልከቻው ጋር ያቀረባቸውን ሠነዶችና የጽሁፍ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ነው (303)2)እና 301(3))።

3.7 ህጉ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም የሚያዝ ካልሆነ በቀር በዚህ ስርዓት በሚሰጠው ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ አይቻልም (309-311 ከተመለከተው በቀር) (ቁ. 306)1)።

3.8 ይግባኝ የሚፈቀድ ከሆነ ይግባኙ ፍርድ በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት (ቁ. 306)2)።

4. <u>ኃላፊነትን ለማስወረድ ስለሚቀርብ አቤቱታ</u>

የሌላው ሰው ወይም የሌሎች ሰዎች መብት የሆነ ሃብት፣ ገንዘብ ወይም ማናቸውም ዓይነት ንብረት በእጅ የሚገኝ ሰው የተባለው ንብረት የኛ ነው በማለት ብዙ ሰዎች የጠየቁት እንደሆነ ኃላፊነቱ ለአንደኛው ወይም ከጠያቂዎቹ መካከል ለተወሰኑ ሰዎች መሆኑን ተረድቶ የተጠየቀውን ነገር ለማስረከብ እንዲችል ተረካቢዎቹ ወይም ባለመብቶቹ ተለይተው እንዲታወቁ ለመወሰን ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ በቁ. 293 እስከ 299 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል ።

ክፍል ሶስት ለጊዜው ስለሚሰጡ ማገጃዎችና ሌሎች ትዕዛዞች (Provisional Remedies)

1. ከፍርድ በፊት ስለሚሰጥ የእስራት ትዕዛዝ (ቁ. 147-150)

1.1 ከሳሹ እንዲሰጥ ለፍ/ቤቱ ማመልከት ይችላል ።

1.2 ማመልከቻው በመሃላ ቃል የተደገፈ መሆን አለበት ።

1.3 ማመልከቻው ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችለው በቁ. 147 (1) (ሀ)ና(ለ) ሥር የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲረጋገጡ ነው ። ሁኔታዎቹም ሀ/ ተከሳሹ በማንኛውም ሁኔታ የዳኝነት ስርዓቱን የሚያሰናክል ድርጊት ሲፈጽም ወይም ለ/ ተከሳሹ ከኢትዩጵያ ግዛት ለመውጣት ሲዘጋጁና መውጣቱም ፍርዱን እንዳይፈጽም የሚያደርገው ሲሆን ነው ።

1.4 ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ከተቀበለ ተከሳሽ ታስሮ እንዲቀርብ ያዛል

1.5 ተከሳሹ የሚፈለግበትን ዕዳ በመያዣ ካስቀመጠ የእስር ትዕዛዙ ተፈፃሚ አይሆንም ።

1.6 ተከሳሹ መያዣውን ካላስቀመጠ ወይም ፍ/ቤት ቀርቦ በቂ ምክንያት ካልሰጠ በቂ መያዣ እንዲያስቀምጥ ወይም ዋስ እንዲጠራ ይታዘዛል ።

1.7 የዋስትናው ወይም የመያዣው ዓይነትና ልክ እንዲሁም ዋስትናው የሚቆይበት ጊዜ በቁ. 148(1) መሠረት ይወሰናል ።

1.8 ተከሳሹን ለማቅረብ ዋስ የሆነ ሰው ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ ተከሳሹ ሊከፍል የሚገባውን ገንዘብ እንዲከፍል ይገደዳል(ቁ. 148(2))።

1.9 በቁ. 149 በተደነገገው መሠረት የዋስትና ግዴታ ሊወርድ ይችላል ዋስትናው ሲወርድ ተከሳሹ ሌላ ዋስ ማቅረብ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ መያዣ ማስቀመጥ አለበት ።

1.10 ተከሳሹ ይህን ግዴታ ለመፈፀም እምቢተኛ ከሆነ እንደሁኔታው እስከ ስድስት ወር በማረፊያ ቤት እንዲቆይ ለማዘዝ ይቻላል (ቁ. 150)። ተከሣሹ አዲስ ዋስ ለመጥራት ወይም መያዣ ለመሰጠት አቅም የሌለው ከሆነ ግን ይህ ትዕዛዝ መሰጠት የለበትም ። ተከሳሹ በማንኛውም ጊዜ ትዕዛዙን ከፈፀመ የማሰር ትዕዛዙ መነሳት አለበት ።

2. <u>ከፍርድ በፊት ንብረትን ማስከበር (ቁ. 151-153)።</u>

2.1 የተከሳሽ ከሳሹ በመጋላ ቃል በተደገፈ አቤቱታ ወይም በሌላ ሁኔታ ማስረዳት ይችላል።

2.2 ፍ/ቤቱ አቤቱታውን መርምሮ እውነት መሆኑን ካረጋገጠ ተከሳሹ ዋስትና እንዲሰጥ ወይም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ንብረት ወይም ግምቱ እንዲቀርብ በወሰነው ጊዜ እንዲያመጣ ወይም ደግሞ ከሚያዘው ገንዘብ ወይም ንብረት ላይ ለሚሰጠው ፍርድ ተመላሽኝ የሚሆን መጠን ያለው ገንዘብ ወይም ንብረት ላይ ለሚሰጠው ፍርድ ተመላሽኝ የሚሆን መጠን ያለው ገንዘብ ወይም ንብረት በፍ/ቤቱ እንዲቀመጥ ወይም ይህን መያዥር የማይሰጥበትን ምክንያት ቀርቦ እንዲያስረዳ ያዛል (ቁ. 151) (1) (ለ)።

2.3 የሚያዘው ንብረት የግድ ከሳሹ ያመለከተው ሁሉ ሳይሆን ከክሱ ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት (ቁ. 151(3)እና (1))። እንዲሁም በቁ. 404 እና በሌላ ህግ እንዳይከበር የተወሰነ ንብረት መያዝ የለበትም።

2.4 ተከሳሹ ዋስ ያልጠራበትን ምክንያት በሚገባ ካስረዳ ወይም የሚፈለግበትን መያዣ ከሰጠ ንብረቱ ይለቀቅለታል ።(ቁ. 152) እና 153(4)።

2.5 ንብረቱ በሚከበርበት ጊዜ የሶስተኛ ወገኖች መብት መጠበቅ አለበት (ቁ. 153) (2) (3)፣ 428 — 421 እና 443)።

3. ለጊዜው የሚሰጥ የማገድ ትዕዛዝ (ቁ. 154-159)።

3.1 በቁ. 154 (ሀ)ና(ለ)። ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች በመጋላ በተደገፈ ቃል ወይም በሌላ መንገድ ሲረጋገጡ ነገሩ በፍርድ እስኪወሰን ድረስ ወይም ሌላ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ክርክር የተነሳበት ንብረት እንዳለ እንዲቆይ፣ ከመጥፋት እንዲድን እንዳይበላሽ ለሌላ ሰው ተላልፎ እንዳይሰጥ ወይም ሌላ ስፍራ እንዳይዘዋወር ወይም እንዳይባክን ፍ/ቤቱ አስፈላጊውን ትዕዛዝ መስጠት አለበት ።

3.2 ውል ወይም ሌላ ግዴታ ተደጋግሞ እንዳይፈርስ ወይም ለማፍረስ የተወሰደው እርምጃ እንዳይቀጥል የሚሰጠው የማገጃ ትዕዛዝ በቁጥር 155 መሠረት ይፈፀማል።

3.3 የማገጃ ትዕዛዝ ያለማክበር የፍትሐብሄርና የወንጀል ኃላፊነትን ሊያስከትል ይችላል(ቁ. 156)።

3.4 የማገጃ ትዕዛዝ መስጠት ያለበት ማመልከቻው ለሌላቸው ወገን ከደረሰው በኃላ ነው ። ከዚህ ውጪ ትዕዛዙ ሊሰጥ የሚችለው መዘግየቱ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል መስሎ ሲታይ ብቻ ነው (ለምሣሌ ንብረቱ የሚጠፋ ወይም የሚበላሽ ሲሆን)።

3.5 የማገጃ ትዕዛዝ በቁጥር 158 በተደነገገው መሠረት ሊነሳ ፣ ሊሠረዝ ወይም ሊሻሻል ይችላል ።

4. ከፍርድ በፊት ስለሚሰጥ ትዕዛዝ (ቁ. 160-165)።

4.1 ለክርክሩ መነሻ የሆነው ወይም የተያዘው ንብረት ክርክሩ እስኪሰማ ቢቆይ የሚበላሽ መሆኑን ወይም መቆየቱ ሌላ ጉዳት ያለው መሆኑን ከተረዳው ፍርድ ቤቱ ንብረቱ እንዲሸጥ ማዘዝ ይችላል ።

4.2 ክርክር የተነሳበትን ሃብት በአንድ ስፍራ አኑሮ መጠበቅ፣ እንዳይበላሽ የሚደረግ ጥንቃቄና የመቆጣጠር ምርምራ በቁጥር 161 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል ።

4.3 በቁጥር 160 እና 161 መሠረት በሚቀርበው አቤቱታ ለፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ከመሰጠቱ በፊት ለሌላኛው ወገን ማስታወቂያ መስጠት አለበት (ቁ. 162)።

ክፍል አራት ፡- ስለፍርድ አፈፃፀም

1.አጠቃላይ ጉዳዬች

1.1 <u>ፍርድን የሚያስፈጽሙ ፍ/ቤቶች</u>

1. ፍርድ የሚያስፈጽመው ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤት ወይም እንዲያስፈጽም የታዘዘ ሌላ ፍ/ቤት ሊሆን ይችላል (ቁ. 371(1))፡፡
2. ሌላ ፍ/ቤት ፍርዱን እንዲያስፈጽም ትዕዛዝ የሚሰጠው በቁ. 372 የተዘረዘሩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ነው ፡፡ ትዕዛዙ የሚሰጠው በፍርድ ባለገንዘቡ ጠያቂነት ወይም ፍርዱን በሰጠው ፍ/ቤት አስተያየት ሊሆን ይችላል ፡፡
3. የፍርድ ማስፈፀም ትዕዛዝ በሚተላለፍበት ጊዜ ትዕዛዙ በቁ. 373 በተደነገገው *መሠረት መፈፀም* አለበት ፡፡
4. ትዕዛዙ የተላለፈለት ፍ/ቤት ስልጣን ዋናውን ፍርድ ከሰጠው ፍ/ቤት ስልጣን *ጋር* እኩል ሆኖ ይቆጠራል ፡፡

1.2 ፍርድ እንዲፈፀም ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1. ፍርድን ለማስፈፀም የሚቀርብ ማመልከቻ በቁ. 378 የተደነገጉትን ፍሬ ነገሮች መያዝ አለበት ።
2. ማመልከቻው እንደ ፍርዱ ብቻ እንዲፈፀምለት የሚጠይቅ እነጂ በዋናው ፍርድ ላይ ያልተገለፀ አዲስ ጥያቄ መጨመር የለበትም ። ፍ/ቤቱም አዲስ ጥያቄ ከቀረበ ማስተናገድ የለበትም / በአፈፃፀም ክርክር ጊዜ የደረሰውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ካልሆነ በስተቀር/
3. ማመልከቻው በድፍኑ እንደ ፍርዱ ይፈፀምልኝ የሚል ሳይሆን እንዲፈፀምለት የሚፈልገውን ጉዳይ በዝርዝርና በግልጽ መያዝ አለበት ።
4. ማመልከቻው ፍርዱ እንደተፈረደ ወዲያውኑ ሊቀርብ ይችላል ። ነገር ግን የፍርድ ባለ ዕዳው እንደ ፍርዱ ለመፈፀም ፈቃደኛ ሆኖ ጊዜ እንዲሰጠው ጠይቆ ቢፈቀድለት ማመልከቻው የሚቀርበው በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ካልፈፀም ነው (ቁ. 378(2))።
5. አንድ የተለየ ነገር እንዲፈፀም ፍ/ቤቱ ከሚሰጠው የማገጃ ትዕዛዝ በቀር ፍርዱ ከተወሰነበት ቀን ጀምሮ አስር አመት ካለፈ የቀረበ የአፈፃፀም ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም ። በተከታታይ የሚፈፀም ግዴታ ከሆነ የአስር ዓመት ጊዜው የሚቆጠረው ግዴታው መፈፀም ከቆመበት ቀን ጀምሮ ነው (ቁ. 384)።
6. የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲቀርብ ማመልከቻው አስፈላጊውን ስረዓት አሟልቶ የቀረበ መሆኑ መረጋገጥ አለበት (ቁ. 385)።
7. ጉድለት ያለበት ከሆነ ማመልከቻው ለባለ ጉዳዩ ይመለስለታል ወይም ተሟልቶ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ያዛል ።
8. ማመልከቻው ተሻሽሎና ተሟልቶ ከቀረበ መጀመሪያ ቀርቦ በነበረበት ቀን ህጋዊ ተቀባይነት እንዳገኘ ይቆጠራል ። / ማመልከቻው መጀመሪያ በቀረበበት እና ተሻሽሎ በቀረበበት ቀን መሀል ያለው ጊዜ ለይርጋ አቆጣጠር ከግምት ውስጥ አይገባም /
9. ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ ከመጥሪያ ጋር ተያይዞ ለፍርድ በለዕዳው ይላክለታል ። የፍርድ ባለዕዳው በመጥሪያው ላይ በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚቃወምበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ይታዘዛል (ቁ.386(11))።

1.3 ፍርድ እንዳይፈፀም የሚታገድበት ሁኔታ

1. በመሠረቱ በአንድ ፍርድ ላይ ይግባኝ መቅረቡ ብቻ ፍርዱ እንዳይፈፀም አያግድም ። ሆኖም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፍርዱ አፈፃፀም ለጊዜው እንዲታገድ ማዘዝ ይችላል ።(ቁ.332)።
2. በመጀመሪያ ደረጃ ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤትም ክርክሩ በይግባኝ ቀርቦ ከመታየቱ በፊት ፍርዱ ቢፈፀም ክርክር በተነሳበት ንብረት ላይ ከፍ ያለ ጉዳት የሚደርስ መሆኑን ከገመተ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተገቢውን ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ፍርዱ እንዳይፈፀም ሊያግድ ይችላል (ቁ. 333)።
3. በቁ. 371 እስከ 376 በተደነገገው መሠረት ፍርዱን እንዲያስፈፅም ለሌላ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሰጥቶ ከሆነ ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤት በቁ. 333 መሠረት የሰጠው የህግ ትዕዛዝ ፍርዱን እንዲያስፈፅም በታዘዘው ፍ/ቤት ላይም ተፈፃሚ ይሆናል (ቁ.376)4/።
4. ፍርዱን እንዲያስፈፅም የታዘዘው ፍ/ቤቱ ራሱ የፍርድ ባለዕዳው በቂ ምክንያት ካቀረበ አቤቱታውን ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት እስኪያቀርብ በቂ ለሆነ ጊዜ ብቻ የሚቆይ የአፈፃፀም ዕገዳ ሊሰጥ ይችላል (ቁ 376(1))።
5. የይግባኝ ባዩ ፍ/ቤት ወይም ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤት ኘሬዛዳንት በቁ. 334 በተደነገገው መሠረት ፍርዱ ለጊዜው እንዳይፈፀም ሊያግዱ ይችላሉ ። ፍ/ቤቱ ቀኑን የሚያረዝም ተጨማሪ ትዕዛዝ ካልሰጠ በቀር ዕገዳው የሚቆየው ለ15 ቀን ብቻ ነው ።
6. በቁ. 332 እስከ 334 በተደነገገው መሠረት ዕገዳ ሊሰጥ የሚችለው በቁ. 335 የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው ።
7. ፍርድ የማገድ ትዕዛዝ የሚሰጠው ማመልከቻው ተከራካሪ ወገኖች ከተሰማ በኃላ ነው ። ሆኖም በመኃላ የተደገፈ ማመልከቻ ከቀረበ ተከራካሪዎቹ ባሉበት ነገሩ እስኪሰማ ድረስ የማገድ ትዕዛዙ ሊሰጥ ይችላል (ቁ. 335(4))።
8. ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በፍርድ ባለገንዘቡ ላይ የፍርድ ባለ ዕዳው ሌላ ክስ ያቀረበበት እንደሆነ ፍርዱን የሚያስፈፅመው ፍ/ቤት ራሱ የፍርድ ባለዕዳው በቂ ዋስትና ወይም መያዣ እንዲሰጥ ካደረገ በኃላ ለክርክሩ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ ፍርዱ ከመፈፀሙ ታግዶ እንዲቆይ ለማዘዝ ይችላል (ቁ.377)።

9. ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች በማናቸውም መንገድ የፍርድ አፈፃፀሙ ካልታገደ / እንዲፈፀም ከታዘዘ/ ይግባኝ ባዩ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በቂ ምክንያት ሲያቀርብለት በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የተወሰደው ነገር እንዲመለስ ዋስትና እንዲሰጥ ወይም የተወሰደውን ንብረት ለመሸፈን የሚችል ግምት ያለው መያዣ እንዳያስቀምጥ ፍ/ቤቱ ለማዘዝ ይችላል (ቁ.336)።

1.4 የፍርድ ባለዕዳውን ስለመመርመር

1. የፍርድ ባለዕዳው በቀረበበት ቀን ፍ/ቤቱና የፍርድ ባለ ገንዘቡ ጥያቄ ያቀርቡለታል። ጥያቄው የሚቀርበውም እንደፍርዱ የማይፈፅምበትን ምክንያት ለማጣራት ነው (ቁ.386(2))።
2. የፍርድ ባለዕዳው ለሚጠየቀው ጥያቄ መልስ የሚሰጠው በጽሁፍ ሳይሆን በቃል ነው ። የሚሰጠው መልስ ወይም መግለጫ እውነት መሆኑን በመኃላ ማረጋገጥ አለበት ።
3. የፍርድ ባለዕዳው የሚያቀርበው ክርክር ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚቃወምበትን ምክንያት የሚያስረዳ / ለምሣሌ በፍርድ የተወሰነው ዕዳ በሚገባ ተከፍሏል ወይም ከፍርድ ባለዕዳነት ነፃ ሆኛለሁ ወይም የፍርድ ባለዕዳነቱን ፈጽሚአለሁ ወይም ፍርዱ በይርጋ ታግዷል እና የመሳሰሉት / ብቻ መሆን አለበት ። በፍርድ ስላለቀው ዋናው ጉዳይ እንደገና መከራከር አይችልም።
4. በፍርድ የተወሰነው ዕዳ በሚገባ ተከፍሏል የሚለው መቃወሚያ ከፍርዱ በኃላ የተከፈለን እንጂ በፊትም ተከፍሎ እያለ በስህተት ተፈርዶብኛል የሚለውን ክረክር አይጨምርም ።
5. የፍርድ ባለዕዳው ካልቀረበ ወይም ቀርቦ በቂ ምክንያት ካልሰጠ ፍርዱ እንዲፈፀም ወዲያውኑ ትዕዛዝ ይሰጣል ። ፍ/ቤቱም ፍርዱ የሚፈፀምበትን ተስማሚ መንገድ ወስኖ የፍርድ ማስፈፀም ትዕዛዝ ለአስፈፃሚው ያስተላልፋል /ቁ. 386/3/፣392/1/፣ 392/3/።
6. የፍርድ ባለዕዳው ፍርዱን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመፈፀም የማይችል ከሆነ ፍርዱ እንዲፈፀም ትዕዛዝ አይሰጥም ። በዚህ ጊዜ በቁ. 387 እና 389 የተደነገጉት የማሰርና በማረፊያ ቤት የማቆየት ትዕዛዞችም ተፈፃሚ አይሆኑም ። ሆኖም ለመፈፀም ችሎት በሚያገኝበት በማናቸውም ጊዜ እንዲፈፅም ማዘዝ ይቻላል ። በዚህ ጊዜ በቁ. 384 የተደነገገው የይርጋ ጊዜም አይቆጠርም ።
7. የፍርድ ባለዕዳው እንዲቀርብ በታዘዘበትን ቀን ካልቀረበ የፍርዱን አፈፃፀም በተመለከተ አስፈላጊውን ትዕዛዝ መስጠት እንጂ ባለዕዳው ታስሮ እንዲቀርብ ትዕዛዝ መስጠት ግዴታ

አይደለም። የማሰር ትዕዛዝ የሚሰጠው በቁ. 386/4/ እና በቁ. 387 በተመለከቱት ሁኔታዎች ብቻ ነው ።

8. በቁ. 386/4/ መሠረት ማመልከቻው የቀረበው ገንዘብ እንዲከፈል የተፈረደ ፍርድ እንዲፈፀም ከሆነና የፍርድ ባለዕዳው በመጥሪያው መሠረት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ታስሮ እንዲቀርብና ለሚደረግለት ጥያቄ ወይም ምርመራ መልስ እንዲሰጥ ፍ/ቤቱ ማዘዝ ይችላል ። የፍርድ ባለዕዳው በቁ. 387 የተመለከተውን ድርጊት ቢፈፅም ባይፈፅምም ፍርዱ ገንዘብ እንዲከፈል የሚያዝ ከሆነ ቁ. 386/4/ ተፈፃሚ ይሆናል ።
9. ቁ. 387 ተፈፃሚ የሚሆነው ፍርዱ ማናቸውም ዓይነት ቢሆን የፍርድ ባለዕዳው ፍርዱ እንዳይፈፀም መሰናክል በመፍጠር ወይም የፍርዱን አፈፃፀም ለማዘግየት ንብረቱን ከፍ/ቤቱ ስልጣን ክልል ውስጥ ለማሸስ ወይም ራሱ ከፍ/ቤቱ ስልጣን ክልል ውስጥ ለመውጣት ለመሸሸና ለመሠወር ያቀደ መሆኑን የሚያረጋግጥ በመኃላ ቃል የተደገፈ ማመልከቻ ሲቀርብ ነው ።
10. በቁ. 386/4/ ወይም 387 መሠረት የማሰር ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ የፍርድ ባለዕዳው የሚፈለግበትን ነገር በፍርዱ መሠረት በፈቃዱ ከፈፀመ የማሰር ትዕዛዝ ተፈፃሚ መሆን የለበትም /ቁ. 388/። ፍ/ቤቱም የማሰር ትዕዛዙ ላይ እንዲሁም የማሰር ትዕዛዙን እንዲያስፈፅም ለታዘዘው ባለስልጣን ይህን ነጥብ ግልጽ ማድረግ አለበት ።
11. የፍርድ ባለዕዳው በደረሰው መጥሪያ መሠረት በራሱ ፈቃድ ከቀረበ ወይም በቁ. 386/4/ ወይም 387 በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ታስሮ ከቀረበና ፍ/ቤቱ በቁ. 386/2/ መሠረት ተገቢውን ምርመራ ከፈፀመ በኃላ የፍርድ ባለዕዳው እንደ ፍርዱ መፈፀም የሚችል ሆኖ ሳለ ያለበቂ ምክንያት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ብቻ የማይፈፅም መሆኑን ከተረዳ የፍርዱ ባለ ዕዳው እስከ ስድስት ወር ድረስ በማረፊያ ቤት ታስሮ እንዲቆይ ሊወሰንበት ይችላል ። ባለዕዳው በሌላ ምክንያት ታስሮ ካለ ግን የማሰር ትዕዛዙ መሰጠት የለበትም/ ቁ. 389/11
12. በቁ. 389/1/ መሠረት የሚሰጠው የእስራት ትዕዛዝ ዓላማው እንደፍርዱ እንዲፈፅም ለማስገደድ ብቻ ነው ። ባለዕዳው የወንጀል ጥፋት ፈጽሞ እንደተቀጣ አይቆጠርም። በሪከርድም አይያዝበትም።
13. በቁ. 389/1/ መሠረት የእስራት ትዕዛዝ ከተሰጠ በኃላ ባለዕዳው እንደ ፍርዱ ቢፈፅም ወይም ባለ ገንዘቡ ከጠየቀ ትዕዛዙ ተፈፃሚ አይሆንም ። ይህ ሁኔታ የተፈፀመው ባለዕዳው እስር ቤት ከገባ በኃላ ከሆነም ከእስራት መልቀቅ አለበት /ቁ.389/2/፣388/2/፣390/1/ ።

14. በቁ. 390/1/ መሠረት ከእስራት የተለቀቀ ባለዕዳ በዚያው ጉዳይ እንደገና መታሰር የለበትም / ቁ. 390/2/፡፡
15. ባለዕዳው መያዙ ወይም ተይዞ መለቀቁ በፍርዱ መሠረት በመሉ ወይም በከፊል ከሚጠየቀው ዕዳ ነፃ አያደርገውም/ ቁ. 391 ፡፡

2. የፍርድ አፈፃፀም ስርዓት

2.1 ጠቅላላ ጉዳዩች

ሀ. ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠ ፍርድ የሚፈፀመው ከቁ. 394 እስከ 398 በተደነገገው መሠረት ነው፡፡

ለ.ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠን ፍርድ ባለዕዳው ገንዘቡን ለፍ/ቤቱ በማስያዝ ወይም ከፍ/ቤት ውጪ ለባለገንዘቡ በመክፈል ወይም እሱም ከባለገንዘቡ የሚፈልገው ገንዘብ ካለ ዕዳውን በመቻቻል ወይም ፍ/ቤቱ በሚሰጠው በሌላ መንገድ መክፈል ይቻላል / ቁ. 395 እስከ 398/፡፡

ሐ. ፍርዱ ገንዘብ እንዲከፈል የሚያዝ ከሆነ ገንዘቡ በሙሉ በአንድ ጊዜ መክፈል አለበት ፡፡ ሆኖም ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤት የመክፈያው ጊዜ እንዲዘገይ ወይም የተወሰነ ገንዘብ በየጊዜው እንዲከፈል በፍርዱ ውስጥ አዞ ከሆነ በዚያው መሠረት መፈፀም አለበት /ቁ. 186/1/፡፡

መ. በፍርድ ላይ ባይገለፅም / ከፍርድ በኃላም ቢሆን/ ፍርዱን የሚያስፈፅመው ፍ/ቤት ራሱ በቁ. 386 ካደረገው ምርመራ ወይም ከፍርድ ባለዕዳው ማመልከቻ በቂ ምክንያት መኖሩን ሲረዳ ወይም የፍርድ ባለገንዘብ ከተስማማ ዕዳው ባንድ ጊዜ ሳይሆን በየጊዜው እንዲከፈል ለማዘዝ ይችላል /ቁ. 186/2/፡፡

ሠ. ከላይ በ/ለ/ ሥር በተመለከተው መንገድ የፍርድ ባለዕዳው ገንዘቡን ካልከፈለ ወይም በ/ሐ/ እና /መ/ በተገለፀው መሠረት ጊዜ ካልተሰጠው ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠውን ውሣኔ የባለዕዳውን ንብረት በማስከበርና በመሸጥ ለማስፈፀም ይቻላል፡፡

ረ. የሚንቀሳቀስ ንብረት እንዲመለስ ወይም እንዲዛወር የተሰጠ ፍርድ የሚፈፀመው ንብረቱን ለፍርድ ባለ መብቱ ወይም ለወኪሉ በማስረክብ ነው /ቁ/399/፡፡

ሰ. የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሆነ ንብረቱን ባለገንዘቡ ወይም ወኪሉ እንዲረከብ ይደረጋል። ፍርድ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የጋራ ባለሀብትነት መኖሩን የሚወስን ከሆነ አመቺ በሆነ መንገድ ፍርድ በህዝቡ እንዲታወቅ በማድረግ ይፈፀማል (ቁ. 402/1/2/።

ሸ. የማይንቀሳቀሰውን ንብረት እንዲያስረክብ የተፈረደበት ወገን ለማስረከብ እምቢተኛ ከሆነ የፍርድ አስፈፃሚው የተዘጋውን ቤት ለመክፈት ወይም ቁልፉን ለመስበር ወይም በማናቸውም ዘዴ የፍርድ ባለመብቱ እንዲረከብ ለማድረግ ይችላል (ቁ. 402/3/)።

ቀ. አንድ ውል እንዲፈፀም ወይም አንድ ነገር እንዳይፈፀም የተሰጠ ትዕዛዝ ሳይከበር በቀረ በቁ. 400 መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል ።

በ. የጽሁፍ ሠነድ እንዲፈረም እንዲረጋገጥ ወይም በሚተላለፉ የገንዘብ ሠነዶች ላይ እንዲፈረም የተሰጠ ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ በቁ. 401 መሠረት ይፈፅማል ።

2.2 ንብረትን ስለማስከበር

ሀ. ንብረት እንዲከበር የሚቀርብ ማመልከቻ በቁ. 379 ሥር የተመለከቱትን ነገሮች አሟልቶ መቅረብ አለበት ።

ለ. መከበር የሚችሉና የማይችሉ እንዲሁም የሚከበሩት ስርዓት ከቁ. 404 እስከ 417 በተደነገገው መሠረት ይመራል።

ሐ. በቁ. 404 ወይም በሌላ ህግ እንዳይከበሩ እና በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት እንዳይወሰዱ የተከለከሉ ንብረቶች መከበር የለባቸውም ።

መ. የሚከበረው ወይም የሚሸጠው ንብረት ግምት በተቻለ መጠን በፍርዱ ላይ ከተገለፀው የገንዘብ ልክ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለበት /ቁ. 394/2/ ። ተመጣጣኝ ያልሆነ ንብረት ካልተገኘ ግን ማንኛውም ንብረት ተከብሮ ይሸጣል እንጂ በዚህ ምክንያት የባለመብቱ መብት መነካት የለበትም።

ሠ. ንብረት ከተከበረ በኃላ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት የሆነው ፍርድ ከተፈፀመ ወይም ፍርዱ የተሻረ ከሆነ ንብረቱ እንዲያዝ የተሰጠው ትዕዛዝ ወዲያው እንደተሻረ ይቆጠራል /ቁ.415/

2.3 በተከበረ ወይም በተያዘ ንብረት ላይ ሶስትኛ ወገኖች የሚያቀርቡት መቃወሚያ

ሀ. በንብረቱ ላይ ቀዳሚ መብት አለኝ የሚሉ ሶስተኛ ወገኖች የንብረቱን መከበር ወይም መያዝ በመቃወም ፍርዱን ለሚያስፈፅመው ፍ/ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ /ቁ.418/።

ለ. በቁ. 418 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ በአፈፃፀም የተያዘው ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ነው እንጂ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት የሆነው ውሣኔ ያለአግባብ የተሰጠ ስለሆነ ይሠረዝልኝ የሚል መሆን የለበትም። ጥያቄው ዋናውን ውሣኔ የሚመለከት ከሆነ ተቃውሞ የሚቀርበውና የሚታየው በቁ. 358 እና በተከታዩቹ መሠረት ነው እንጂ በቁ. 418 አይደለም

ሐ. በቁ. 418 መሠረት የሚቀርበው ማመልከቻ በቂ ባልሆነ ምክንያት ከዘገየ ተቀባይነት አይኖረውም ። መዘግየቱ የሚወሰነው እንደ ነገሩ አከባቢ ሁኔታ ነው ። ሆኖም ንብረቱ ከተሸጠ በኃላ መቅረብ አይችልም / በቁ. 445 የተደነገገው እንደተጠበቀ ነው /

ፍ/ቤቱ ማመልከቻውንና ማስረጃውን ከመረመረ በኃላ አቤቱታውን መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል /ቁ. 419/።

ፍ/ቤቱ ማመልከቻውን ውድቅ ካደረገው አመልካቹ ለክርክሩ መነሻ በሆነው ንብረት ላይ አዲስ ክስ ማቅረብ ይችላል /ቁ.401/ ። ሁኔታው የሚፈቅድ ከሆነም በቁ.358 መሠረት መቃወሚያ ማቅረብ ይችላል ።

ረ. የተያዘው ወይም የተከበረው ንብረት የሶስተኛ ወገን የመያዣ መብት ያለበት ከሆነ የሶስተኛ ወገኖች መብት ተጠብቆ አፈፃፀሙ ይቀጥላል እንጂ በዚህ ምክንያት ንብረቱ እንዲከበር የተሰጠው ትዕዛዝ አይሰረዝም ። ንብረቱን ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በህብረት የያዙትና ያልተከፋፈሉት ከሆነ ከተካፋዩቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ መቅረብ ይችላል /ቁ. 420 እና 443/

2.4 ለፍርድ አፈፃፀም ንብረትን የመሸጥ ስ/ስርዓት

1. የመሸጥ ስ/ስርዓቱ ከቁ. 422 እስከ ቁ.449 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል ።
2. ከቁ. 422 እስከ 431 የተደነገጉት በሁሉም የሽያጭ ዓይነቶች ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ ናቸው ።
3. ከቀ.432 እስከ 438 ያሉት በተለይ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ብቻ የሚመለከቱ ናቸው ።
4. ከቁ.439 እስከ 449 ያሉት በተለይ የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን የሚመለከቱ ናቸው
5. ማንኛውም ንብረት በአፈፃፀም የሚሰጠው በሐራጅ ሽያጭ ነው ። ሆኖም በፍርድ ባለዕዳውና ባለገንዘቡ ስምምነት ንብረቱ በግል ወይም በስምምነት እንዲሸጥ ፍ/ቤቱ ለማዘዝ ይችላል ።
6. ንብረቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ከተወሰነ የሽያጩ ማስታወቂያ ለህዝብ መገለጽ አለበት ማስታወቂያውም ንብረቱ በሚገኝበት አቅራቢያ ወይም ግልጽ ሆኖ ሊታወቅና ሊሰማ በሚችልበት ዘዴና በማናቸውም ልማዳዊ ዓይነት ባደባባይ በመንገር ወይም በመለጠፍ

ሊፈጽም ይችላል (ቁ. 425/1)፡፡ እና 414(2)፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ማስታወቂያው በጋዜጣ መውጣት አለበት / ቁ. 425/2/፡፡

7. ማስታወቂያው በቁ. 423 ሥር የተዘረዘሩትን መግለጫዎች አሟልቶ መያዝ አለበት ፡፡
8. የፍርድ ባለዕዳው ከዚህ አስቀድሞ እንዲሸጥ ካልተስማማ በቀር የሚንቀሳቀስ ንብረት ማስታወቂያው ከወጣበት ቀን አንስቶ 15 ቀን የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሆነ ደግሞ 30 ቀን ሳይቆይ በሐራጅ ሊሸጥ አይችልም (ቁ. 426)፡፡
9. ነገር ግን ንብረቱ ቶሎ የሚበላሽ ከሆነ ወይም ለጥበቃው የሚያስፈልገው ወጪ ከዕቃው ዋጋ የሚበልጥ ከሆነ ከላይ የተጠቀሰውን ጊዜ መጠበቅ ሳያስፈልግ ንብረቱ ወዲያውኑ ሊሸጥ ይችላል /ቀ. 426፣406/2/
10. የሐራጅ ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት የፍርድ ባለዕዳው የሚፈለግበትን ዕዳ በመሉ ከከፈለ የሐራጅ ሽያጭ ይቆማል /ቁ. 427/፡፡
11. በመጀመሪያው ጨረታ ማስታወቂያ ላይ በተገለፀው የዋጋ ግምት ንብረቱን የሚገዛ ገዥ ካልተገኘ ሁለተኛ ጨረታ እንዲደረግ ይታዛዛል (ቁ.428)፡፡
12. ሁለተኛው የሽያጭ ስነ- ስርዓት የሚፈፀመው ለመጀመሪያው ጨረታ በተደነገገው ስርዓት መሠረት ነው (ቁ. 428/1/)፡፡ ሆኖም ግን የጨረታ መነሻ ዋጋ የሚሆነው የመጀመሪያው ጨረታ ግምት ሳይሆን ከዚያ በታችም ቢሆን በሁለተኛው ጨረታ ንብረቱ የሚሸጠው ከቀረቡት ተጫራቾች ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርበው ተጫራች ነው ፡፡
13. የሚንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ ሲሸጥ ሽያጩ ከስርዓት ውጪ መፈፀሙ ሽያጩን አያፈርሰውም ፡፡ ሆኖም ጉዳት የደረሰበት ወገን ጉዳቱ አድራሹ ካለ እንዲከፍለው መጠየቅ ይችላል /ቁ.435/ ፡፡
14. የማይንቀሳቀስ ንብረት በሐራጅ ሲሸጥ ከስነ- ስርዓት ውጪ የተፈፀመ ከሆነ ግን የፍርድ ባገንዘቡ ወይም መብቱ የሚገባው ሌላ ሰው ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ መጠየቅ ይችላል ፡፡ ሽያጩ የሚፈርሰው ከስርዓት ውጪ ስለተፈፀመ ብቻ ሳይሆን ግዙፍ የሆነ ጉድለት ወይም የማታለልና የማጭበርበር ሥራ ተፈፅሞ ሲገኝና ይህም በአመልካቹ ላይ ቀጥተኛ ጉዳት ያደረሰበት መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው / ቁ. 445/፡፡
15. እንዲሸጥ የተወሰነው የማይንቀሳቀስ ንብረት ከመሸጡ በፊት በዚሁ ንብረት ላይ መብት ያገኘ ሰው ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲናተገድ ማመልከት ይችላል /ቁ.44/፡፡
16. የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲሸጥ ከታዘዘ በኃላ የፍርድ ሳለዕዳው ያነኑ ንብረት በማከራየት ወይም በሌላ መንገድ ዕዳውን ለመክፈል እንደሚችል ማረጋጋጫ ካቀረበ ፍ/ቤቱ በቂ ጊዜ ሰጥቶት ሽያጩ ለጊዜው እንዲታገድ ለማዘዝ ይችላል / ቁ. 439/፡፡

17. በፍርድ ምክንያት ንብረት እንዲተላለፍ የተሰጠውን ትዕዛዝ የመቃወም ወየም የእምቢተኝነት ድርጊት ሲፈፅም ፍ/ቤቱ ከቁ. 450 እስከ 455 በተደነገገው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል ።

ክፍል አምስት ፣ ልዩ ልዩ ጉዳዮች (Miscellaneous Issues)

1. ዳኝነት ሳይከፈልበት በነፃ ስለሚቀርብ ክስ

1. በመሠረቱ ማንኛውም ክስ /የተከሳሽ ከሳሽነት ክስን ጨምሮ/ ተገቢው ዳኝነት ካልተከፈለበት በቀር ተቀባይነት አያገኝም።
2. ሆኖም ግን ዳኝነት መክፈል የማይችል ድሃ ሰው የዳኝነት ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ሳይከፍል የነፃ ፋይል ማስከፈት ይችላል /ቁ. 467/።
3. ማመልከቻው የሚቀርበው በመኃላ ተደግፎ መሆን አለበት /ቁ. 468/።
4. ማመልከቻው መቅረብ ያለበት ዋናውን ክስ ለሚያየው ፍ/ቤት ራሱ ነው ፣። ከቀበሌ መስተዳድር የሚሰጠው የድህነት ማስረጃ በቁ. 472 መሠረት ለፍ/ቤቱ እንደ ማስረጃ የሚቀርብ ነው እንጂ እራሱን ችሎ የፍ/ቤቱን ውሣኔ የሚተካ አይደለም።
5. ፍ/ቤቱ የቀረበውን ማመልከቻና የአመልካቹን ቃል ከመረመረ በኃላ እንዲሁም አመልካቹ ሀብት አለው የሚሉ ስዎች እንዳሉ ቀርበው እንዲያስረዱ ካደረገና የሁለቱንም ወገን ማስረጃዎች ከሰማና ከመረመረ በኃላ ማመልከቻውን መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል ።
6. ማመልከቻው ተቀባይነት ካጣ በዚያው ጉዳይ ለሁለተኛው ጊዜ በነፃ ልከራከር የሚል ማመልከቻ ማቅረብ አይቻልም /ቁ. 477/
7. ማመልከቻውን ካገኘ ለአመልካቹ የምሰክር ማስረጃ ይሰጠዋል። የቀረበው ክስ ዳኝነት እንደተከፈለበት እንደማንኛውም ክስ በመደበኛው ስነ/ ስርዓት ይመራል/ቁ. 473/
8. ማስረጃው የሚያገለግለው በነፃ እንዲታይ ፈቃድ ለተሰጠበት ክርክር ብቻ ነው /ቁ. 474/2/
9. የምስክር ማስረጃው በነፃ እንዲታይ የተፈቀደው ክርክር የመጨረሻ ፍርድ ውሣኔ እስኪያገኝ ወይም ዋጋ የለውም ተብሎ እስኪዘጋ ድረስ የሚፀና ሆኖ ያገለግላል።

10. በይግባኝ ደረጃ ማስረጃው የሚያገለግለው በነፃ እንዲከራከር የተፈቀደለት ወገን መልስ ሰጪ ሲሆን ነው ። ይግባኝ ባይ ከሆነ አይገለገልበትም። ሆኖም በነፃ የይግባኝ መዝገብ እንዲከፈትለት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማመልከት ይችላል /ቁ. 474/
11. በቁ. 475 በተመለከቱ ሁኔታዎች ማስረጃው ዋጋ ሊያጣ ይችላል ።
12. በነፃ የተከራከረው ወገን በክሱ በረታ ጊዜ ክርክሩ የተነሳበትን ንብረት ከመረከቡ በፊት የዳኝነቱ ገንዘብ ከሀብቱ ተቀንሶ ገቢ መሆን አለበት /ቁ. 476/
13. በነፃ የተከራካሪው ወገን በክሱ ቢረታም ቢሸነፍም ማስረጃው በተሰጠው በአስር ዓመታት ውስጥ ወይም ክርክሩ በሚቀጥልበት ጊዜ ሀብት ካገኘ ይህንኑ አስታውቆ ዳኝነቱን መክፈል አለበት /ቁ.478/።

2. <u>አቤቱታን ስለማሻሻል</u>

ሀ. ማሻሻያው የክሱን ወይም የመከላከያውን አቤቱታ በማብራራት ክርክሩን በተሻሻለ ሁኔታ የሚገልጽ እና ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ሆኖ ከተገኘ በተከራካሪዎቹ ጥያቄ ወይም በፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ማንኛውም አቤቱታ ሊሻሻል ይችላላ /ቁ. 91/።
ለ. ማሻሻያው መከናወን ያለበት ከፍርድ በፊት ነው ።
ሐ. አቤቱታው ሲሻሻል ፍ/ቤቱ ስለኪሳራው አስፈላጊውን ትዕዛዝ መስጠት አለበት
መ. የክሱ መሻሻል ነገሩን በመጀመሪያ ከቀረበለት ፍ/ቤት ስልጣን በላይ ያደረገው ከሆነ የመጀመሪያው ፍ/ቤት ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ያስተላልፋል ። ጉዳዩ የተላለፈለት ፍ/ቤትም የነገሩን መስማት ይቀጥላል።

3. <u>ስለ ጊዜ አወሳሰንና ስለቀጠሮ</u>

ሀ. አንድ ነገር የሚፈፀምበት ጊዜ በሀግ ካልተወሰነ ፍ/ቤት የነገሩን ሁኔታ በማየት በቂ መስሎ የታየውን ጊዜ መወሰን ይችላል /ቁ. 192/1/።
ለ. በህግ የተወሰነውን ጊዜ ግን በሌላ አኳኋን ተገልጾ ካልተወሰነ በቀር ማሣጠር ወይም መሠረዝ አይቻልም /ቁ. 192/2።
ሐ. በህግ የተወሰነውን ሳይሆን በፍ/ቤት የተሰጠውን ጊዜ በከባድ ምክንያት ብቻ ማስረዘም ይቻላል /ቁ. 194 እና 196/ ።
መ. ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት በሌለበት ሁኔታ አንድ ነገር እንዲፈፀም ከተወሰነው ጊዜ በኃላ ቢፈፀም እንዳልተፈፀመ ሆኖ ይቆጠራል /ቁ. 195/ ።
ሠ. ክርክሩ በሚሰማበት ጊዜ አንድን ጉዳይ ለመፈፀም ቀጠሮ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለመፈፀም በቂ ሆኖ የሚገመት ጊዜ በመወሰን ቀጠሮ ይሰጣል /ቁ. 197/1//

ረ. ምስክር መስማት የተጀመረበት ክርክር ሲሆን ለምስክርነት የተጠሩትን ሁሉ ሰምቶ እስኪጨርስ ፍ/ቤቱ በየዕለቱ አዳሪ የሚሆን ቀጠሮ እየሰጠ ስራውን ማከናወን አለበት /ቁ. 297/3///።

ሰ. የተከራካሪዎቹ ወገኖች ጠበቃ ወይም ነገረ ፈጅ ባለመቅረቡ ምክንያት ቀጠሮ አይሰጥም /ቁ. 197/4/።

ሸ. ለቀጠሮው ምክንያት የሆነው ጉዳይ ሳይፈፀም የቀረው ከተከራካሪዎቹ ወገኖች በአንደኛው ጉድለት የሆነ እንደሆነ ጉዳዩ ባይፈፀምም ፍ/ቤቱ የጉዳዩን መፈፀም ሳይጠብቅ በዚያው ቀነ ቀጠሮ የመሰለውን ውሣኔ ለመስጠት ይችላል /ቁ. 199/1/።

ቀ. ጉዳዩ ሳይፈፀም የቀረው በተከራካሪዎቹ ጉድለት ካልሆነ ግን ፍ/ቤቱ ሌላ ቀጠሮ መስጠት አለበት /ቁ. 199/2/።

4. <u>በኪሣራ ስለሚከፈል ገንዘብ የሚሰጥ ዋስትና</u>

ሀ. ተከሳሹ ለደረሰበት ወይም ሊደርስበት ይችላል ተብሎ ለሚገመተው ኪሣራ ከሳሹ በቂ መያዣ የመስጠት ወይም ዋስ የመጥራት ግዴታ አለበት /ቁ. 201/1/።

ለ. ይህን ግዴታ አለመፈፀም መዝገቡን ያዘጋል ፣ቁ.201/1//

ሐ. ከሳሽ መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ውስጥ የተዘጋው መዝገብ እንዲከፈትለት ማመልከት ይችላል /ቁ.201/2/

መ. ከሳሽ ዋስ ወይም መያዣ ያላቀረበው በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ ፍ/ቤቱ ስለኪሳራው መያዣና ዋስትና ተገቢውን ትዕዛዝ ከሰጠ በኃላ መዝገቡን ከፍቶ ክርክሩን ለመስማት ቀጠሮ ይሰጣል ።

5. <u>ስለወጪና ስለኪሣራ</u>

ሀ. ወጪና ኪሣራ የሚወሰነው ብቁ. 462 - 466 በተደነገገው መሠረት ነው ።

ለ. ፍ/ቤቱ ህጉን ተከትሎ መወሰን አለበት ። በደፈናው ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ ማለት አግባብ አይደለም ።

ሐ. ረቺው ያቀረበውን የወጪ ዝርዝርና ማስረጃ እንዲሁም ግራ ቀኙ የሚያደርጉትን ክርክር ከመረመረ በኃላ ፍ/ቤቱ አስፈላጊውን ውሣኔ ይሰጣል /ቁ. 463 እና 464/።

መ. በቁ. 463 እና 464 መሠረት ከሚወሰነው ወጪና ኪሳራ በተጨማሪ በቁ. 465 በተዘረዘሩ ሁኔታዎች ፍ/ቤቱ ለተጎጂው ካሣ መወሰን ይችላል ። ወጪና ኪሳራውን ሳይጨምር የሚፈረደው ካሣ ከ500 ብር መብለጥ የለበትም።

ሠ. በወጪውና ኪሣራው ውሣኔ ላይ ብቻ ይግባኝ መጠየቅ ይቻላል /ቁ. 466/።

6. **ፍርድን ወይም ትዕዛዙን የሰጠው ፍ/ቤት ራሱ የሚፈፅማቸው ማረሚያዎች ወይም ማስተካከያዎች (Review by court of Rendition)**

ሀ. **ከስነ- ስርዓት ውጪ የተፈፀሙ ጉዳዩች** ፡- አንዳንድ ከስርዓት ውጪ የተፈፀሙ ጉዳዩችን ወይም ስህተቶችን ለማረም ይግባኝ መውሰድ ሳያስፈልግ ከቁ. 207-212 በተደነገገው መሠረት ፍ/ቤቱ በራሱ ጊዜ ወይም በባለጉዳዩቹ ጥያቄ ስህተቱን ለማረም፣ ለመሠረዝ ወይ ለመዘጋት ይችላል ።

ለ. **ጉዳዩን እንደገና ማየት**

1. በአንቀጽ 6 መሠረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን እንደገና ለማየት ይችላል
2. ሆኖም ይህን ጥያቄ ማቅረብ የሚቻለው በአንቀጽ 6 ስር በተደነገጉት ውስን ሁኔታዎች ብቻ ነው።
3. የመጨረሻ ውሣኔ ያገኙ ጉዳዩች እንደገና እንዳይታይ የሚከለክለው አንቀጽ 5 (Res judicata) በአንቀጽ 6 የተመለከተውን መብት አያግድም።

ሐ. **ስለ መቃወም** (Opposition)

1. በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም ለመግባት የሚችልና ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ሰው ፍርዱን መቃወም ይችላል / ቁ. 358/
2. መቃወሚያው መቅረብ ያለበት ፍርዱ ከመፈፀሙ በፊት ነው / ቁ. 358/
3. መቃወሚያው የሚቀርበው በቁ. 359 የተደነገገውን ፎርም ተከትሎ መሆን አለበት
4. መቃወሚያው ሲቀርብ ፍ/ቤቱ በመጀመሪያው ክርክር ተካፋይ የነበሩትን ወገኖች አስቀርቦ ከመረመረ በኃላ መቃወሚያ የቀረበበትን ፍርድ ለማጽደቅ፣ ለማሻሻል ፣ለመለወጥ ወይም ለመሰረዝ ይችላል ።/ቁ. 360/

መ. **ተከሳሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሣኔ ስለማንሳት**

1. በሌለበት የተፈረደበት ተከሳሽ ውሣኔው መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ውስጥ ቀርቦ ውሣኔው እንዲነሳለት ሊያመላክት ይችላል /ቁ. 78/
2. ተከሳሽ የጥሪው ትዕዛዝ በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን ወይም ክርክሩ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን ቀረቦ መከላከያውን ያላሰማው ወይም መልስ ያልሰጠው በበቂ ምክንያት መሆኑን ካስረዳ ፍ/ቤቱ ውሣኔውን ሊያነሳለት ይችላል

7. ፍ/ቤትንና ችሎትን ስለማስከበር

ሀ. **አስተዳደራዊ እርምጃ**

1. የማናቸውም ፍ/ቤት ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ የፍርድ ቤቱንና የዳኝነት አካሄድ ስነ ስርዓት ለማስከበር ማናቸውንም አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ ሊወሰድ ይችላል/ቁ. 480/ ።
2. የሚወሰደው እርምጃ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ የሆነው ማናቸውም እርምጃ ሲሆን አጥፊውን መገሰጽ፣ ማረም፣ መምከር፣ ማስጠንቀቅ ወይም ከችሎት እንዲወጣ ማዘዝ ሊያጠቃለል ይችላል ።
3. አጥፊውን መሳደብ፣ ማዋረድና ማንቋሸሽ እንዲሁም ሰብአዊ መብቱንና ክብሩን የሚነካ እርምጃ መውሰድ ስህተት ነው ።
4. የሚወሰደው እርምጃ የዳኝነት ሥራ አካሄድንና ፍ/ቤቱን ለማስከበር ብቻ የታለመ መሆን አለበት ።

ለ. **የገንዘብ ቅጣት**

1. ከተፈፀመው ጥፋት ጋር ሲመዛዘን ከላይ በ"ሀ" ሥር የተጠቀሰውን አስተዳደራዊ እርምጃ ብቻ መውሰድ የዳኝነት አካሄድ ስርዓቱን ወይም የፍ/ቤቱን ክብር ለመጠበቅ በቂ ሆኖ ካልታየው ፍ/ቤቱ በያዘው መዝገብ ላይ የገንዘብ መቀጫ በአጥፊው ላይ ሊወሰንበት ይችላል /ቁ. 480/
2. በዚህ መልክ የሚወሰነው ቅጣት እንደ ወንጀል ቅጣት የሚቆጠር ስላልሆነ የወንጀል አንቀጽ መጥቀስ አስፈላጊ አይደለም።

ሐ. **የወንጀል ቅጣት**

1. በወንጀለኛ መቅጫ ህግ በቁጥር 442 እስከ 447 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የወንጀል ተግባር የተፈፀመ እንደሆነ ጥፋቱ በተደረገበት ጊዜ ፍ/ቤቱ በያዘው በፍትሐብሄር መዝገብ ላይ ቀጥታ ቅጣት ሊወሰን ይችላል /ቁ. 481/
2. ወዲያው (Summarily) የቅጣት ውሣኔ እንዲሰጥ የሚፈቅደው ስርዓት የተቀጪውን የመከላከል መብት የሚያስቀር ስለሆነ ፍ/ቤቱ ይህን ስልጣን ውስን በሆኑ ሁኔታዎችና በጥንቃቄ መጠቀም ይኖርበታል።
3. ወዲያው መቅጣት የሚችለውም፡-

ሀ. የዳኝነት ስርዓቱ በመፈፀም ላይ ሳለ ጥፋቱ ሲፈፀም ዳኛው ራሱ ያየ ወይም የሰማ ሲሆን(flagrant cases)፣ እና

ለ. ወዲያው እርምጃ ካልተወሰደ የዳኝነት ስርዓቱ የሚረበሽ ሲሆን መሆን አለበት ።

4. ሁኔታው ወዲያው ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችል ከሆነ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ከመወሰኑ በፊት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት ። በተለይም የአጥፊውን ዕድሜ፣ የትምህርትና የኑሮ ሁኔታ፣ ባህል፣ አስተዳደግ፣ አካባቢ እና ሌሎችንም ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት ። ይህም የሚጠቅመው አጥፊው ድርጊቱን የፈፀመው ሆነ ብሎ የዳኝነት ስርዓቱን ለማሳሳት ወይም ለማወክ መሆኑን ወይም ባለማወቅ የፈፀመው መሆኑን ለመለየት ነው ። ባለማወቅ የተፈፀመ ከሆነ በምክር ወይም በማስጠንቀቂያ ብቻ ማለፍ በቂ ሊሆን ይችላል ።
5. በተጨማሪም ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ከመወሰኑ በፊት
   - አጥፊውን ማስጠንቀቅ፣
   - ተገቢ መስሎ ከታየው ከችሎት እንዲወጣ ማዘዝ፣
   - ከተፈፀመው ድርጊት ጋር ሲነፃፀር ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ወይም ከችሎት እንዲወጣ ማዘዙ ብቻውን በቂ ካልሆነ አግባብነት ባለው የወ/መ/ህግ በመጥቀስ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ መስጠት ።
6. ወዲያው (summarily) በተሰጠው ውሣኔ ላይ ተቀጪው ይግባኝ መጠየቅ ስለሚችል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን በአግባቡ መመርመር ይችል ዘንድ ቅጣቱን የሚወሰነው ፍ/ቤት የተፈፀሙውን ጥፋት / ድርጊት ከሆነ የተፈፀመውን ድርጊት ቃል ከሆነ የተባለውን ቃል/ በዝርዝርና በትክክል መግለጽ አለበት ። ጥፋተኛው ችሎት ደፍሯል ወይም ዳኛውን ሰድቧል ወይም ችሎቱን አውኳል የሚሉ ድፍን አገላለፆችን መጠቀም የለበትም።
7. የተፈፀመው ጥፋት ቀጥታ ከዳኛው ክብርና መልካም ስም ጋር የተያያዘ ግላዊ ፀባይ ያለው ከሆነ አጥፊው ካልተስማማ በስተቀር ጉዳዩን ሌላ ዳኛ ቢያየው ይመረጣል።
8. ጥፋቱ የተፈፀመው ወዲያው እርምጃ መውሰድ በሚቻልበት ሁኔታ ካልሆነ ወይም የሚቻል ቢሆንም በፍ/ቤቱ አስተያየት ጉዳዩ ላይ ወዲያው ውሣኔ መስጠቱ ለፍትህ አሰጣጥ ተገቢ መስሎ ካልታየው ፍ/ቤቱ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ጉዳዩን ማጣራት አለበት ። እንዲሁም አጥፊው ራሱን እነዲከላከል መፍቀድ አለበት ።

8. የዳኝነት ስነ ምግባር

ሀ. አንድ ዳኛ በአጠቃላይ

1. ከአደሉ ነፃ ሆኖ መስራት፣
2. የዳኝነት ነፃነትና ክብርን መጠበቅ ፣
3. የህግ የበላይነትን ተግባራዊ ማድረግ፣

4. ሰብዓዊ መብቶችን መጠበቅና ማክበር፣
5. የዳኝነት ነፃነትና ክብርን ለመጠበቅ ይችል ዘንድ በዳኝነት ስራውም ሆነ በግል ህይወቱ አርአይነት ያለው ከፍተኛ ስነ ምግባር ማሣየት አለበት ።

ለ. በተለይም ከችሎት አካሄድ ጋር በተያያዘ፣

1. ተከራካሪዎች ሁሉ በእኩልነት ማየትና መብታቸውን በእኩልነት መጠበቅ፣
2. በቂ ባልሆነ ምክንያት ቀጠሮ አለማብዛት
3. በችሎት አመራሩ የፍ/ቤቱን ክብር መጠበቅ
4. አብረውት ከሚያስችሉት ዳኞችና ከሌሎች የሥራ ባልደረቦቹ ጋር ተግባብቶ ፣ ተባብሮና ተከባብሮ መስራት፣
5. ክርክሮችን በትዕግስት ማዳመጥና ማስጨረስ፣
6. የባለጉዳዩችን ሰብዓና፣ መብትና ክብር መጠበቅ፣
7. ተከራካሪዎችን በአግባቡ መቆጣጠር ተገቢ ያልሆኑ ጠባይ ሲያሳዩ በአግባቡ መገሰጽ፣ ማረም እና አስፈላጊም ሲሆን አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ፣
8. አንድን ጉዳይ እንዳያይ በህግ የተከለከለ ከሆነ መቃወሚያ እስኪቀርብበት ሳይጠብቅ ምክንያቱን በሚገባ ገልፆ ከችሎት መነሳት አለበት ።

ሐ. ከላይ የተጠቀሱት የስነ ምግባር ጉዳዩች በፊዲራሉ ወይም በየክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በሚወጡት የስነ ምግባር ደንቦች የሚታዩ ይሆናል።

የይግባኝ ክርክሮች ስርዓተ- ችሎት

መግቢያ ፡-

ይህን ስርዓተ- ችሎት (Bench- Book) ለማዘጋጀት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት በዕለት ተዕለት የችሎት አካሄድ ስርዓት ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሁኔታዎችን ዳኛው በቀላሉና በፍጥነት ሊፈታ የሚችልበትን ማጣቀሻ (guideline) ለማዘጋጀት ነው ። ስርዓተ- ችሎቱ መደበኞቹን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሀግና የፍ/ሥ/ሥ/ህግ የሚተካ አይደለም። በሥ/ሥ/ህጎቹ ውስጥ የተካተቱትን ጉዳዩች በሙሉ የያዘም አይደለም።

የዚህ ስርዓተ- ችሎት ዋና መሠረት የሥ/ሥ/ህጎች ሆነው ነገር ግን፡-

1. በስ/ስርዓት ህጎች ውስጥ የተካተቱ ሆነው ነገር ግን ጠቅለል ባለ አገላለጽ የተደነገጉ በመሆናቸው ማብራሪያ የሚሹ ጉዳዩችን ለማብራራት ተሞክሯል ።
2. በህጉ በግለጽ ያልተሸፈኑ ነገር ግን በዕለት ተዕለት የፍ/ቤቶች ሥራ ውስጠ በብዛት የሚያጋጥሙ የስነ ስርዓት ጉዳዩችን በተመለከተ ያለውን ክፍተት ለመሙላት ጥረት ተደርጓል።
3. በስነ- ስርዓት ህጎቹ የተሸፈኑ ሆነው ነገር ግን በአተረጓጎምና በአተገባበር ረገድ በፍ/ቤቶች ወይም በዳኞች መካከል ልዩነት የሚታይባቸውን ዋና ዋና የስነ- ስርዓት ጉዳዩች በተመለከተ በተቻለ መጠን ልዩነቶቹ የሚጠቡበትንና ህጎቹ በተመሣሣይ ሁኔታ የሚተረጐሙበትንና የሚተገበሩበትን አቅጣጫ ለማሣየት ተሞክሯል።

ከላይ እንደተገለፀው የስርዓተ - ችሎቱ ዋና መሠረት የሥ/ስርዓት ህጎቹ ቢሆኑም ማብራሪያ የሚሹ ነጥቦችን ለማብራራትና ክፍተቶችን ለመሙላት ግን ልምድ ያላቸው ዳኞችን፣ ጠበቆችንና ሌሎች የህግ ሰዎችን በቃልና በጽሁፍ በመጠየቅና በማማከር የተገኙ ሃሣቦች እንዲሁም የሌሎች ሀገሮች ልምዶች እንደመነሻ ሃሣብ በጥቅም ላይ ውለዋል።

ስርዓተ- ችሎቱ እንደ ህግ አዛዥነት ባይኖረውም እንደቀላል ማጣቀሻ፣ እንደማብራሪያና እንደ ክፍተት መሙያ ግን ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ይታመናል።

ክፍል አንድ ፣ የፍትብሄር ይግባኝ

1. መደበኛ ሁኔታዎች

1.1 ይግባኝ ስለሚፈቀድበት ሀኔታ እና ይግባኝ ለመስማት ስልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች

ሀ. በህግ ካልተከለከለ በቀር ይግባኝ መጠየቅ መብት ነው /ቁ. 320/

ለ. ይግባኝ የሚቻለው በመጨረሻ ፍርድ ላይ ነው ።

ሐ. ውሣኔውን የሰጠው ፍ/ቤት ራሱ የሚፈፅማቸው የማሻሻያ፣ እንደገና የማጣሪያ ወይም የማረም ስርዓቶች በሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች ይህ ስርዓት ሳይፈፀም ይግባኝ መጠየቅ አይቻልም /ቁ. 320/2/።

መ. ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ (Interlocutory matters) ላይ ይግባኝ መጠየቅ አይቻልም ። ሆኖም ከዚህ ትዕዛዝ ጋር የተያያዘውን ቅሬታ ከስረ ነገሩ ይግባኝ ጋር ማቅረብ ይቻላል / ቁ. 320/3/ እና 211/1/።

ሠ. ጊዜያዊ አገልግሎት ያለው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ የሚከለክለው ድንጋጌ ማንም ሰው እንዲታሰር ወይም በማረፊያ ቤት ተይዞ እንዲቆይ ወይም ከስረ ነገሩ በፊት በእጅ ያለውን ንብረት ለሌላው ወገን እንዳያዛውር በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ከማቅረብ አያግደውም/ቁ.320/4/።

ረ. ይግባኝ ለመቀበል ስልጣን ያላቸውን ፍ/ቤቶችና ሁለተኛ ይግባኝ የሚቀርብበትን ስርዓት በተመለከተ የፊደራል ፍ/ቤቶች በአዋጅ ቁ. 25/88 / እና ማሻሻያዎቹ/ የሚታይ ሲሆን የክልል ፍ/ቤቶችን በተመለከተ በክልሉ ህግ የሚታይ ይሆናል ።

1.2 <u>ይግባኝ ስለሚቀርብበት ጊዜ</u>

ሀ. የይግባኝ አቤቱታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባው ይግባኝ በሚባልበት ጉዳይ ላይ ፍርድ በተሰጠ በ60 ቀን ውስጥ ነው / 323/2/።

ለ. ይህ ጊዜ ካለፈ የይግባኝ ማመልከቻው ተቀበይነት አይኖረውም ። ሆኖም ከቁ. 324-326 በተደነገገው መሠረት ይግባኝ ባዩ የማስፈቀጃ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል ። ፍ/ቤቱም የይግባኝ ማመልከቻውን ጊዜው በማለፉ አልቀበለውም ብሎ ሲመልስ ይግባኝ ባዩ በ10 ቀን ውስጥ የማስፈቀጃ ማመልከቻ ማቅረብ እንደሚችል ሊነግረው ይገባል /ቁ.224፣11//

ሐ. የማስፈቀጃው ማመልከቻ በቁ. 325 መሠረት መቅረብ አለበት ።

መ. ፍ/ቤቱ መልስ ሰጪውን አስቀርቦ የሁለቱንም ወገን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ማመልከቻውን መቀበል ወይም ውድቅ ማድረግ ይችላል /ቁ. 325/3/እና 326/።

ሠ. ማመልከቻው ተቀባይነት የለውም ተብሎ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ አይፈቀድም /ቁ. 326/3//።

1.3 <u>የይግባኝ ማመልከቻ ይዘት</u>

ሀ. ዳኝነት ሳይከፍል በነፃ እንዲከራከር ካልተፈቀደለት በቀር /ቁ. 424/ይግባኝ ባዩ ተገቢውን ዳኝነት መክፈል አለበት ።

ለ. የይግባኝ ማመልከቻው በቁ. 327 የተመለከቱትን ነገሮች ማሟላት አለበት ።

ሐ. ማመልከቻው በክርክር መልክ ሳይሆን ፍርዱን የሚቃወምበትን ምክንያት በአጭሩ በመዘርዘር አርዕስትና ተራ ቁጥር ተሰጥቶበት መቅረብ አለበት /ቁ.328/።

መ. ማመልከቻው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያልተነሳውን አዲስ ክርክርና ማስረጃ መያዝ የለበትም። ፍ/ቤቱም ይህን መቀበል የለበትም ቁ. 329/።

ሆኖም ይግባኝ ባዩ በቁ. 327/3/ መሠረት አዲስ ማስረጃ እንዲቀርብለት ካመለከተ ፍ/ቤቱ በቁ. 345 መሠረት ሊፈቅድለት ይችላል ። የማስረጃው አቀባበል ስነ- ስርአት በቁ 346 መሠረት ይፈፅማል ።

ረ. ህጉ የማያዘውን ፎርምና ይዘት ባለሟሟላቱ ተቀባይነት ያጣ የይግባኝ ማመልከቻ ተሻሽሎ መቅረብ ይችላል /ቁ. 329/2/፣330/።

1.4 <u>ይግባኙን ስለመቀበል</u>

ሀ. ፍ/ቤቱ የይግባኝ ማመልለቻውንና ይግባኝ ባይ ወይም ጠበቃው በቃል የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኃላ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠበትን የመዝገብ ግልባጭ መርምሮ ፍርዱ ጉድለት የሌለበት መሆኑን ከተረዳው መልስ ሰጪውን ሳይጠራ ይግባኙን ዘግቶ አቤት ባዩን ሊያሰናብት ይችላል /ቁ. 337/።

ለ. በቁ. 337 መሠረት ይግባኙን ለመዝጋት የሚሰጠው ትዕዛዝ ጉዳዩች ውስጥ ሳይገባ ይግባኙ ውድቅ መሆኑን ብቻ በአጭሩ የሚገልጽ መሆን አለበት ።

ሐ. ፍ/ቤቱ ይግባኙን ውድቅ ካላደረገው / ከተቀበለው/ ይግባኙ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ወስኖ መልስ ሰጪው እንዲቀርብ መጥሪያውንና የይግባኝ ማመልከቻውን ይልክለታል ።

1.5 <u>ይግባኙን ለመስማት በተቀጠረበት ቀን የባለጉዳዩቹ አለመቅረብ</u> ።

ሀ. ግራ ቀኙ ከቀሩ የይግባኝ መዝገቡ ይዘጋል /ቁ. 69/2/።

ለ. መልስ ሰጪው ቀርቦ ይግባኝ ባዩ ከቀረ የይግባኝ መዝገቡ ይዘጋል /ቁ.73።

ሐ. መልስ ሰጪው መጥሪያ ደርሶት ከቀረ ክርክሩ በሌለበት ይቀጥላል /ቁ. 338 እና 70/4/፡፡

መ. መልስ ሰጪው የቀረው መጥሪያ ያልደረሰው በመሆኑ ወይም መጥሪያው የደረሰው በቂ ባልሆነ ጊዜ ውስጥ ከሆነ ሁለተኛ መጥሪያ ይላክለታል /ቁ. 70/ለ/ሐ/፡፡

ሠ. መጥሪያው ያልደረሰው በይግባኝ ባዩ ችልተኝነት ከሆነ የይግባኝ መዝገቡ ይዘጋል /ቁ.70/መ//፡፡

ረ. ከላይ በ/ሀ/፣/ለ/ እና /ሠ/ በተገለፀው መሠረት የይግባኝ መዝገብ ከተዘጋ ይግባኝ ባዩ በቁ. 74 በተገለፀው መሠረት ችግሩን ካስረዳ መዝገቡ ሊከፈትለት ይችላል ፡፡

1.6 <u>ይግባኙን ስለመስማት</u>

ሀ. ይግባኙ በሚሰማበት ጊዜ ይግባኝ ባዩ አስቀድሞ የቃል ክርክርሩን ይጀምራል/ቁ. 339/1/፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተለይ ካልፈቀደ በቀር ይግባኝ ባዩ በይግባኝ ማመልከቻው ላይ ዘርዝሮ ያልገለፀውን አዲስ ነገር በማንሳት የቃል ክርክሩን ማቅረብ አይችልም /ቁ.328/2/፡፡

ለ. ይግባኝ ባዩ የቃል ክርክሩን ካሰማ በኃላ ቅሬታው መሠረት የሌለው መሆኑን ፍ/ቤቱ ከተረዳ የመልስ ሰጪውን ክርክር መስማት ሳያስፈልግ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ወዲያው ሊሰርዘው ይችላል /ቁ. 339/2/፡፡

ሐ. ይግባኙ ወዲያው ካልተሰረዘ መልስ ሰጪው የመከላከያ መልሱን በቃል ያሰማል ፡፡ ቀጥሎም ይግባኝ ባዩ የመልስ መልሱን በቃል ክርክር ያቀርባል /ቁ. 339/3/፡፡

መ. በመሠረቱ መልስ ሰጪው መልሱን በቃል ክርክር ማቅረብ አለበት ፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ መስሎ ከታየው የመከላከያ መልሱ በጽሁፍ እንዲቀረብ ማዘዝ ይችላል /ቁ. 339/3/፡፡

ሠ. ይግባኝ ባዩ ባቀረበው የይግባኝ መዝገብ ላይ መልስ ሰጪው የራሱ የይግባኝ ቅሬታ / / ማቅረብ ይችላል /340//

ረ. የይግባኝ ክርክሩ ካለቀ በኃላ ፍ/ቤቱ ውሣኔ ይሰጣል ፡፡

1.7 <u>ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፡-</u>

1.7.1 <u>ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት፡-</u>

ሀ. በቁ. 345 እና 346 በተደነገገው መሠረት ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችል ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይቻላል ፡፡

ለ. በቁ. 341 መሠረት ጉዳዩን ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መመለስ ይችላል፡፡ በዚህ ቁጥር መሠረት ጉዳዩ ሲመለስ በክርክሩ ላይ ውሣኔ የሚሰጠው የመጀመሪያው ፍ/ቤት ራሱ ነው ፡፡

ሐ. በቁ. 343 መሠረት የነገሩን ጨብጥ አስተካክሎ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መመለስ ይችላል፡፡ በዚህ ቁጥር መሠረት ጉዳዩ ሲመለስ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ መጣራት ያለባቸውን ነጥቦች

አጣርቶ ውጤቱን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይልካል እንጂ በዋናው ክርክር ላይ እራሱ የመጨረሻ ውሣኔ አይሰጥም ።

1.7.2 **<u>ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ራሱ ይግባኙን ሲወስን</u>** ፡-

ሀ. ይግባኝ የቀረበበትን ፍርድ ወይም ውሣኔ ለማጽናት ፣ ለመለወጥ ወይም ለመሻር ይችላል /ቁ. 348/1///።

ለ. ፍርዱን የሚሰጠው ከይግባኝ ክርክሩ የተገኙትን መረጃዎች፣ ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ የወሰነውን ፍርድ ቤት መዝገብ/ እንዳስፈላጊነቱ/ እና የራሱን መዝገብ ከመረመረ በኃላ ነው / ቁ. 347፣342/።

ሐ. ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ የሰጠው ፍ/ቤት ያየዘውን ጭብጥ ብቻ ለመከተል ሳይገደድ በመዝገቡ ላይ በተረዳው መሠረት በመሰለው መንገድ ጭብጡን ለውጦ ወይም አሻሽሎ መወሰን ይችላል /ቁ. 342፣328/3/፣182/።

መ. ይግባኝ ተከራካሪዎቹ ወገኖች በይግባኝ በሚሰጠው ውሣኔ በሚይዘው ጉዳይ ወይም በሚሰጠው ትዕዛዝ የተስማሙ መሆናቸውን በጽሁፍ ያቀረቡለት እንደሆነ ውሣኔው ወይም ትዕዛዙ የሚሰጠው ተከራካሪዎቹ በተስማሙበት መሠረት ሊሆን ይችላል/ 348/2/።

ሠ. በቁ. 320/3/ እና 211/1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ይግባኝ በተባለበት ጉዳይ ላይ የተፈፀመውን ማንኛውንም የስነ- ስርዓት ጉድለት በራሱ አስተያየት ሊያርም ይችላል ። እንዲሁም ያገጠመው የስነ- ስርዓት ጉድለት ለትክክለኛው ፍርድ አሰጣጥ ተቃራኒ መስሎ ከታየው የተፈረደው ፍርድ እንዳልተፈረደ ተቆጥሮ እንደገና እንዲታይ ትዕዛዝ ይሰጣል /211/2/።

2. ሌሎች ጉዳዬች (Miscellaneous Issues)

ሀ. ስለ ወጪና ስለ ኪሣራ

ሀ. ይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤት መልስ ሰጪው እንዲቀርብ ከማዘዙ በፊት ወይም ቀረቦ ሲያመለክት ይግባኝ ባዩ ያቀረበው ይግባኝ ወይም የመጀመሪያው ክርክር ወየም ሁለቱም ክርክሮች በመልስ ሰጪው ላይ ስለሚያደርሱት ኪሣራና ስለማንኛውም ወጭ በቂ የሚሆን የኪሣራ መያዣ ወይም ዋስ እንዲሰጥ ለማዘዝ ይችላል /ቁ.202/1/።

ለ. ይግባኝ ባዩ ክርክር ከተነሳበት ንብረት በቀር ሌላ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሌለው እንደሆነ እና የሚኖረው ከኢትዮጵያ ግዛት ውጭ የሆነ እንደሆነ ምንጊዜም ቢሆን ይግባኝ ባዩ መያዣ ወይም ዋስ እንዲሰጥ መታዘዝ አለበት/ቁ. 202/2/።

ሐ.የተጠየቀው መያዣ ወይመ ዋስትናው ፍርድ ቤቱ በወሰነው ጊዜ ውስጥ ሳይሰጥ የቀረ እንደሆነ የቀረበው ይግባኝ እንዲዘጋ ትዕዛዝ ይሰጣል /ቁ. 202/3/።

መ. ይግባኙ በተዘጋ በአንድ ወር ውስጥ መዝገቡ እንዲከፈትለት ይግባኝ ባዩ ባለመለከ ጊዜ በቁ.202/2/ የተደነገገው ተፈጻሚ ይሆናል ።

ሠ. ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ዋናው የይግባኝ ክርክር ላይ ውሣኔ ከሰጠ በኃላ ወጪና ኪሳራን በተመለከተም አስፈላጊውን ውሣኔ መስጠት አለበት ። በዚህም ጊዜ በቁ. 462 እስከ 465 ያሉት ድንጋጌዎች እንዳስፈላጊነቱ ተፈፃሚ ይሆናል ።

ረ. ማንኛውም ተከራካሪ ወገን በስረ ነገሩ ላይ ይግባኝ ባያቀብልም በተወሰነበት የወጭ ወይም የኪሣራ አከፋፈል ብይን ላይ ይግባኝ ለመጠየቅ ይችላል ። በዚሁም ነገር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል /ቁ. 466/።

ለ. ዳኝነት ሳይከፈልበት በነፃ ስለሚቀርብ ይግባኝ

ሀ. በመጀመሪያው ክርክር ከሳሹ ዳኝነት ሳይከፍል በነፃ እንዲከራከር የድህነት ምስክር ማስረጃ ተሰጥቶት ከሆነ ማስረጃው የሚፀናው በነፃ እንዲታይ የተፈቀደው ክርክር የመጨረሻ ፍርድ ውሣኔ እስኪያገኝ ወይም ዋጋ የለውም ተብሎ እስኪዘጋ ድረስ ነው /ቁ. 474/2/።

ለ. በይግባኝ ደረጃ ማስረጃው የሚያገለግለው በነፃ እንዲከራከር የተፈቀደለት ወገን መልስ ሰጪ ሲሆን ነው ። ይግባኝ ባይ ከሆነ አይገለገልበትም። ሆኖም በነፃ የይግባኝ መዝገብ እንዲከፈትለት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል /ቁ. 474/2/።

ሐ. ስለቀጠሮ አሰጣጥ

ሀ. ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝን ለመስማት የሚሰጠው የቀነ ቀጠሮ አወሳሰን ስርዓት የሚፈፀመው የፍ/ቤቱን የሥራ መጠን፣ በአጀንዳው ላይ ያለውን የቀጠሮ ብዛት፣ መልስ ሰጪው መከራከሪያውን ለማቅረብ የሚችልበት በቂ ጊዜ የሚያገኝ መሆኑን፣ የአድራሻውን ርቀትና ቅርበት ሁኔታ መሠረት አድርጎ በመገመት ነው የቁ. 338/2/፡፡

ለ. በተጨማሪም ከቁ. 292 እስከ 299 የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው በይግባኝ ደረጃም ተፈፃሚ መሆን ይችላሉ /ቁ. 79/2/፡፡

መ. ፍ/ቤቱንና ችሎትን ስለማስከበር

1. አስተዳደራዊ እርምጃ

1. የማናቸውም ፍ/ቤት ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ የፍርድ ቤቱንና የዳኝነት አካሄድ ስነ ስርዓት ለማስከበር ማናቸውም አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል /ቁ. 480/፡፡
2. የሚወሰደው እርምጃ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ የሆነው ማናቸውም እርምጃ ሲሆን አጥፊውን መገሰጽ፣ ማረም፣መምከር ፣ ማስጠንቀቅ ወይም ከችሎት እንዲወጣ ማዘዝ ሊያጠቃልል ይችላል ፡፡
3. አጥፊውን መሳደብ፣ ማዋረድና ማንቋሸሽ እንዲሁም ሰብአዊ መብቱንና ክብሩን የሚነካ እርምጃ መውሰድ ስህተት ነው ፡፡

2. የገንዘብ ቅጣት

1. ከተፈፀመው ጥፋት ጋር ሲመዛዘን ከላይ በ"1" ስር የተጠቀሰውን አስተዳደራዊ እርምጃ ብቻ መውሰድ የዳኝነት አካሄድ ስርዓቱን ወይም የፍ/ቤቱን ክብር ለመጠበቅ በቂ ሆኖ ካልታየው ፍ/ቤቱ በያዘው መዝገብ ላይ የገንዘብ መቀጫ በአጥፊው ላይ ሊወስንበት ይችላል /ቁ. 480/፡፡
2. በዚህ መልክ የሚወሰነው ቅጣት እንደ ወንጀል ቅጣት የሚቆጠር ስላልሆነ የወንጀል አንቀጽ መጥቀስ አስፈላጊ አይደለም፡፡

3. የወንጀል ቅጣት

1. በወንጀለኛ መቅጫ ህግ በቁጥር 442 እስከ 447 የተመለከቱተን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የወንጀል ተግባር የተፈፀመ እንደሆነ ጥፋቱ በተደረገበት ጊዜ ፍ/ቤቱ በያዘው በፍትሐብሄር መዝገብ ላይ ቀጥታ ቅጣት ሊወሰን ይችላል /ቁ. 481/፡፡

2. ወዲያው (summarily) የቅጣት ውሣኔ እንዲሰጥ የሚፈቅደው ስርዓት የተቀጪውን የመከላከል መብት የሚያስቀር ስለሆነ ፍ/ቤቱ ይህን ስልጣን ውስን በሆኑ ሁኔታዎችና በጥንቃቄ መጠቀም ይኖርበታል ።

3. **ወዲያው መቅጣት የሚችለውም፡-**

   ሀ. የዳኝነት ስርዓቱ በመፈፀም ላይ ሳለ ጥፋቱ ሲፈፀም ዳኛው ራሱ ያየ ወይም የሰማ ሲሆን (flagrant cases)

   ለ. ወዲያው እርምጃ ካልተወሰደ የዳኝነት ስርዓቱ የሚረበሽ ሲሆን መሆን አለበት ።

4. ሁኔታው ወዲያው ውሣኔ ለመስጠት የሚያስችል ከሆነ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ከመወሰኑ በፊት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት ። በተለይም የአጥፊውን ዕድሜ፣ የትምህረትና የኑሮ ሁኔታ፣ ባህል፣ አስተዳደግ፣ አካባቢ እና ሌሎችንም ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት ። ይህም የሚጠቅመው አጥፊው ድርጊቱን የፈፀመው ሆነ ብሎ የዳኝነት ስርዓቱን ለማሳሳት ወይም ለማወክ መሆኑን ወይም ባለማወቅ የፈፀመው መሆኑን ለመለየት ነው ። ባለማወቅ የተፈፀመ ከሆነ በምክር ወይም በማስጠንቀቂያ ብቻ ማለፍ በቂ ሊሆን ይችላል።

5. በተጨማሪም ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ከመወሰኑ በፊት፣

   - አጥፊውን ማስጠንቀቅ፣
   - ተገቢ መስሎ ከታየም ከችሎት እንዲወጣ ማዘዝ፣
   - ከተፈፀመው ድርጊት ጋር ቢነፃፀር ማስጠንቀቂያ መስጠቱ ወይም ከችሎት እንዲወጣ ማዘዙ ብቻውን በቂ ካልሆነ አግባብነት ባለው የወ/መ/ህግ በመጥቀስ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሣኔ መስጠት ።

6. ወዲያው (summarily) በተሰጠው ውሣኔ ላይ ተቀጪው ይግባኝ መጠየቅ ስለሚችል ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን በአግባቡ መመርመር ይችል ዘድ ቅጣቱን የሚወሰነው ፍ/ቤት የተፈፀመውን ጥፋት / ድርጊት ከሆነ የተፈፀመውን ድርጊት ቃል ከሆነ የተባለውን ቃል/ በዝርዝርና በትክክል መግለጽ አለበት ። ጥፋተኛው ችሎት ደፍሯል ወይም ዳኛውን ሰድቧል ወይም ችሎቱን አውኳል የሚሉ ድፍን አገላለፃችን መጠቀም የለበትም።

7. የተፈፀመው ጥፋት ቀጥታ ከዳኛው ክብርና መልካም ስም ጋር የተያያዘ ግላዊ ፀባይ ያለው ከሆነ አጥፊው ካልተስማማ በስተቀር ጉዳዩን ሌላ ዳኛ ቢያየው ይመረጣል።

8. ጥፋቱ የተፈፀመው ወዲያው እርምጃ መውሰድ በሚቻልበት ሁኔታ ካልሆነ ወይም የሚቻል ቢሆንም በፍ/ቤቱ አስተያየት ጉዳዩ ላይ ወዲያው ውሣኔ መስጠቱ ለፍትህ

አሰጣጥ ተገቢ መስሎ ካልታየው ፍ/ቤቱ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ገዳዩን ማጣራት አለበት ። እንዲሁም አጥፊው ራሱን እንዲከላከል መፍቀድ አለበት ።

ሠ. የዳኝነት ስነ ምግባር

ሀ. አንድ ዳኛ በአጠቃላይ

1. ከአድልዎ ነፃ ሆኖ መስራት፣
2. የዳኝነት ነፃነትና ክብርን መጠበቅ፣
3. የህግ የበላይነቱን ተግባራዊ ማድረግ
4. ሰብዓዊ መብቶችን መጠበቅና ማክበር፣

ክፍል ሁለት የወንጀል ይግባኝ

1. ይግባኝ ለመቀበል ስልጣን ያላቸው ፍ/ቤቶች

ሀ. የፊዴራል ፍ/ቤቶችን በተመለከተ ይግባኝ የማየት ስልጣናቸው እና ሁለተኛ ይግባኝ ሊቀረብ የሚችልበት ሁኔታ በአዋጅ ቁ. 25/88 እና በማሻሻያዎቹ መሠረት የሚታይ ይሆናል።

ለ. የክልል ፍ/ቤቶች የይግባኝ ስልጣን እና ሁለተኛ ይግባኝ የሚቀርብበት ሁኔታ በክልሉ ህግ መሠረት የሚታይ ይሆናል ።

2. የይግባኝ መብት

ሀ. በህግ ካልተከለከለ በስተቀር ይግባኝ መጠየቅ መብት ነው ።

ለ. ዓ/ህጉ ወይም የግል ከሳሹ ፍርድ ቤት በሰጠው ለጊዜው የመልቀቅ ወይም ነፃ የመልቀቅ ፍርድ ላይ ወይም ቅጣቱ በቂ አይደለም በማለት ይግባኝ መጠየቅ ይችላል /ቁ. 185/2/

ሐ. የተፈረደበት ሰው የጥፋተኝነት ውሣኔ በተሰጠበትና በቅጣቱ ይግባኝ ለመጠየቅ ይችላል /ቁ.185/1።

መ. ተከሳሹ የተከሰበሰበትን ወንጀል አምኖ በእምነቱ መሠረት ጥፋተኝነቱ ከተወሰነ በኃላ ስለቅጣቱ ልክ ወይም ህጋዊነት ካልሆነ በቀር በጥፋተኝነት ውሣኔው ላይ ይግባኝ መጠየቅ አይችልም /ቁ.185/1/። ሆኖም ግን ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት ተከሳሹ ህጉ በሚይዘው መሠረት /ቁ. 134/1/ ድርጊቱን መፈፀሙን ሙሉ በሙሉ ባላመነበት ሁኔታ ወይም በቁ. 134/2/ ወይም 133/2/ መሠረት ዓ/ህጉ ማስረጃውን እንዲያሰማ ማዘዝ በነበረበት ሁኔታ ያለአግባብ ተከሳሹ እንዳመነ ቆጥሮ የጥፋተኝነት ውሣኔ ቢሰጥና ተከሳሹም ይህን ነጥብ መሠረት አድርጎ በጥፋተኝነት ውሣኔ ላይ ይግባኝ ቢጠይቅና የሥር ፍ/ቤት የፈፀመው ስህተት ሌላ ማስረጃ መስማት ሳያስፈልግ ፍ/ቤቱ ከመዘገበው ዝርዝር ላይ ግልጽ ሆኖ የሚታይ ከሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ አይቶ ውሣኔውን በመሻር በጉዳዩ ላይ ማስረጃ ተሰምቶ ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለመጀመሪያው ፍ/ቤት መመለስ ይችላል ። ቁ. 185/1/ ተከሳሹ ሙሉ በሙሉ አምኖ የተቀጣበትን እንጂ እንዲህ አይነቱን ይግባኝ የመከልከል ዓላማ የለውም።

ሠ. ጊዜያዊ ትዕዛዞች ላይ ይግባኝ መጠየቅ አይቻልም። ነገር ግን የጥፋተኝነት ውሣኔ ወይም ለጊዜው በመልቀቅ ወይም ነፃ በመልቀቅ በተሰጠ ፍርድ ላይ ይግባኝ ከተጠየቀ እነዚህን ነጥቦች የይግባኝ ቅሬታ ነጥብ አድርጎ ማቅረብ ይቻላል/ቁ. 184/።

ረ. በቁ. 184 ስር የተዘረዘሩት ይግባኝ የማይፈቀድባቸው ትዕዛዞች ዝርዝር ሙሉ ዝረዝር (exhaustive list) አይደለም ። በዝርዝሩ ውስጥ በግልጽ ባይቀመጥም አንድ ትዕዛዝ በባህሪው

ጊዜያዊ አገልግሎት ብቻ ያለው ከሆነ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የቀረበን ይግባኝ ላለመቀበል ይችላል። ምክንያቱም ይግባኝ መጠየቅ የሚቻለው በጥፋተኝነት ውሣኔ፣ ለጊዜው በመልቀቅ ወይም ነፃ በመልቀቅ በተሰጠ ውሣኔ ወይም በቅጣት ውሣኔ ላይ ነው /ቁ. 181 እና 185/።

3. የይግባኝ ማመልከቻ

ሀ. ይግባኝ ባዩ ወይም ጠበቃው ይግባኝ የሚልበት ፍርድ በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ ይግባኝ ማለቱን የሚያስታውቅ ማመልከቻ/Notice of appeal/ ማቅረብ አለበት ፣ቁ. 187/1/።

ለ. የይግባኝ ማመልከቻው ፍርድ ተገልብጦ በተሰጠ በ30 ቀን ውስጥ ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት መዝገብ ቤት መቅረብ አለበት /ቁ. 187/2/።

የይግባኝ ማመልከቻ ይግባኝ በተባለበት ፍርድ ላይ ያሉትን የመቃወሚያ ምክንያቶች ባጭሩ ለይቶ ትችት ሳይጨመርበት በተራ ቁጥር በዝርዝር መግፍ አለበት ። ይግባኝ ባዩ እንዲወሰንለት የሚፈልገውን ፍርድ በማመልከቻው ላይ በግልጽ ማስቀመጥ አለበት /ቁ. 189/1/።

መ. ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ የሰጠው ፍርድ ቤት የይግባኝ ማመልከቻ እንደደረሰው 15 ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመዝገቡን ግልባጭ ከይግባኝ ማመልከቻው ጋር ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መላክ አለበት /ቁ. 190/1/። ሆኖም መዝገቡን መገልበጥ ጉዳዩን የሚያዘገየው ከሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ዋናው መዝገብ እንዲቀርብለት ለማድረግ ይችላል/ቁ. 190/2/።

4. ጊዜው ያለፈበት የይግባኝ ማመልከቻ

ሀ. ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ የሰጠው ፍ/ቤት የይግባኝ ማስታወቂያው ወይም ማመልከቻው ጊዜው ካለፈ በኃላ ከቀረበለት አልቀበልም ማለት አለበት ። ከዚያም አመልካቹ ይግባኝ እንዲፈቀድለት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የማስፈቀጃ ማመልከቻ እንዲያቀረብ ይነገረዋል/ቁ.191/1/።

ለ. ፍርዱን የሰጠው ፍ/ቤት ጊዜው ያለፈበትን የይግባኝ ማስታወቂያ ወይም የይግባኝ ማመልከቻ አልቀበልም ማለት ሲገባው ተቀብሎ የላከው እንደሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ራሱ ማመልከቻውን አልቀበልም በማለት የማስፈቀድ ማመልከቻ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል።

ሐ. የማስፈቀጃ ጥያቄው ከቀረበ በኃላ የይግባኝ ጊዜው ያለፈው በአመልካቹ ጥፋት ሳይሆን በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍ/ቤቱ ከተረዳ ይግባኙ እንዲሰማ በመወሰን የይግባኙ ማመልከቻ የሚቀርብበትን ቀን ይወስናል ።

መ. የማስፈቀጃ ማመልከቻ ሲቀረብ በዚህ ጉዳይ ላይ የመልስ ሰጪውን ክርክር መስማት ሳያስፈልግ ፍ/ቤቱ አመልካቹ ያቀረበውን አቤቱታና ማስረጃ ብቻ በማየት አስፈላጊውን ውሣኔ ለመስጠት ይችላል ።

5. ፍርድ እንዳይፈፀም ስለማገድ

ሀ. ይግባኝ ባዩ ይግባኙ ከመሰማቱ በፊት በማንኛውም ጊዜ ወይም ይግባኙ በሚሰማበት በማንኛውም ጊዜ ፍርዱ እንዲታጋድለት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማመልከት ይችላል /ቁ. 188/5//።

ለ. ተከሳሹ ይግባኙ እስኪወሰን ድረስ በዋስ የተለቀቀ እንደሆነ የእስራቱ ቅጣት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ አይጀመርም /ቁ. 188/2//።

ሐ. ዋስትና የሚፈቀድበት ሁኔታና የዋስትናው መጠን ከቁ. 63 እስከ 79 በተደነገገው መሠረት የሚታይ ይሆናል።

መ. ሆኖም ተከሳሹ የተፈረደበት መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለየት ባለ ጥንቃቄ ማየት ያስፈልጋል ። በመሆኑም ይግባኝ ባዩ በዋስ ቢለቀቅ የማይጠፋ መሆኑን ማረጋገጥ እንዲሁም ይግባኙ ታይቶ የይግባኝ ባዩ ቅጣት የመሻሻል ወይም ከእስራት ውጪ በሆነ ሌላ ቅጣት የመቀየር ዕድልን በመጠኑም ቢሆን የይግባኝ መዝገቡን አይቶ ማጣራት ያስፈልጋል ።

ሠ. የሞት ፍርድ ላይ ይግባኝ ሲጠየቅ ይግባኝ ባዩ በዋስ መለቀቅ የለበትም። ሆኖም ይግባኙ ታይቶ ውሣኔ እስኪያገኝ ወይም ርዕሰ ብሄሩ ውሣኔውን አይተው ሳባቸውን እስኪገልፁ ድረስ ቅጣቱ ተፈፃሚ መሆን የለበትም/ቁ. 204/።

ረ. ይግባኝ የተባለበት ፍርድ እንዲፈፀሙ ያዘዛቸው የጥንቃቄ ትዕዛዞች ይግባኝ የተባለባቸው ቢሆኑም መፈፀም አለባቸው /ቁ. 188/3//።

ሰ. ስለ ካሳ ወይም ስለ ኪሣራ ወጪ የተሰጠ ፍርድም ከመፈፀም አይታገድም/ቁ. 188/4//።

6. ተከሳሹ ይግባኝ ሳይጠይቅ ዓ/ህግ ብቻ ይግባኝ ሲጠይቅ ይግባኙ ውሣኔ እስኪያገኝ ድረስ ተከሳሹ / መልስ ሰጪው/ የሚቆይበት ሁኔታ

ሀ. ተከሳሹ በተፈረደበት የእስራት ውሣኔ ላይ ይግባኝ ሳይጠይቅ ዓ/ህግ ቅጣቱ አንሷል ብሎ ይግባኝ ከጠየቀ ተከሳሹ በዋስትና መለቀቅ የለበትም።

ለ. ተከሳሹ ነፃ በወጣበት ወይም ከእስራት ውጪ የሆነ ውሣኔ በተሰጠበት ፍርድ ላይ ዓ/ህጉ ይግባኝ በጠየቀ ጊዜ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የወንጀሉን ከባድነት ፣ ተከሳሹ ሊጠፋ የሚችልበትን ዕድል እንዲሁም ይግባኙ ታይቶ የጥፋተኝነት ውሣኔ ሊሰጥ ወይም ቅጣቱ ሊጨመር የሚችልበትን ዕድል ሊወሰን የሚችለውን የቅጣት ዓይነት ከግምት ውስጥ

በማስገባት እንደ ሁኔታው ይግባኝ እስኪታይ ድረስ ተከሳሹ ወህኒ ቤት እንዲቆይ ወይም በቂ ዋስትና እንዲያቀረብ ወይም ያለዋስትና እንዲቆይ ለማዘዝ ይችላል፡፡

7. ይግባኙን መስማት

ሀ. ይግባኙ በጊዜው የቀረበ እንደሆነ ወየም ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ እንዲሰማ ፍ/ቤቱ የፈቀደ እንደሆነ ፍ/ቤቱ የይግባኝ ማመልከቻውን ከተቀበለ በኃላ ይግባኙ የሚሰማበትን ቀን ወስኖ ለነገርተኞቹ ይነግራል/ቁ.192/፡፡

ለ. በወንጀል ይግባኝ ላይ መልስ ሰጪው ሳይጠራ ይግባኙ አያስቀርብም ብሎ መዝጋት አይቻልም ፡፡

ሐ. ተከሳሹ ወይም ዓ/ህጉ ይግባኝ ጠይቀው ይግባኙን ለመስማት በተቀጠረበት ቀን ሳይቀርቡ ከቀሩ ይግባኙ ይሰረዛል ፡፡ ሆኖም ያልቀረቡት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ካረጋገጠ መዝገቡ እንደገና ተከፍቶ ይግባኙ እንዲሰማ ማድረግ ይቻላል/ቁ. 193/፡፡

መ. መልስ ሰጪው ካልቀረበ የይግባኙ መሰማት መልስ ሰጪው በሌለበት ይቀጥላል፡፡

ሠ. ይግባኙ በሚሰማበት ጊዜ ይግባኝ ባዩ በመጀመሪያ ይግባኙን በቃል ያስረዳል ፡፡ ይግባኝ ባዩ ከገለፀው ሁኔታ ይግባኙ መሠረት የሌለው መሆኑን ፍ/ቤቱ ከተረዳ በነገሩ ውስጥ መግባትና የመልስ ሰጪውን ክርክር መስማት ሳያስፈልግ ይግባኙን መሠረዝ ይችላል /ቁ.195/1//፡፡

ረ. ይግባኝ ባዩ ቅሬታውን በአግባቡ ካስረዳና ፍ/ቤቱም በጉዳዩ ውስጥ ለመግባት በቂ ምክንያት ያለ መሆኑን ከተረዳ መልስ ሰጪውም ክርክሩን በቃል እንዲሰጥ ያደረጋል ፡፡ ይግባኝ ባዩም የመልስ መልስ የመስጠት መብት አለው /195/1/ እና 192/፡፡

8. የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ስልጣን

ሀ. የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተጨማሪ ማስረጃ የሚያስፈልግ መስሎ ከታየው ምክንያቱን በመመዝገብ ማስረጃውን መቀበል ይችላል /ቁ. 194/፡፡

ለ. ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ተጨማሪ ማስረጃ ታዞ እንደሆነም ማስረጃውን ከሰማ በኃላ /ቁ. 195/2/

1. ተከሳሹን ነፃ በመልቀቅ ወይም ለጊዜው በመልቀቅ በተሰጠ ትዕዛዝ ይግባኝ የተባለ እንደሆነ ትዕዛዙን ሰርዞ ስልጣን ያለው ሌላ ፍ/ቤት ነገሩን እንደገና እንዲያይ ማዘዝ ወይም እራሱ ጥፋተኛ ነው ብሎ ሊፈርድበት ይችላል፡፡
2. ጥፋተኛ ነው በተባለበት ውሣኔ እና በቅጣቱ ይግባኝ በተባለ ጊዜ፡-

   ሀ. ውሣኔውን ሰርዞ ተከሳሹን በነፃ ለመልቀቅ ይችላል ፡፡ ወይም

ለ. ፍርዱን ለውጦ ወይም ሳይለወጥ ቅጣቱን ያፀናል ፣ ይጨምራል ወይም ይቀንሳል። ሆኖም ዓ/ህግ በጠየቀው ይባኝ ላይ ተከሳሹ ይግባኝ ሳይጠይቅ ፍርዱን ሰርዞ ተከሳሹን ነፃ መልቀቅ ወይም ቅጣቱን መቀነስ እንዲሁም ተከሳሽ ብቻ ይግባኝ ጠይቆ ዓ/ህግ ሳይጠይቅ ተከሳሹን በሚጎዳ ሁኔታ ፍርዱን መለወጥ ወይም ቅጣቱን መጨመር አይችልም።

3. ጥፋተኛ ነው በተባለበት ውሣኔ ላይ ብቻ ተከሳሹ ይግባኝ ሲጠይቅ ፍርዱንና ቅጣቱን ሰርዞ ተከሳሹን በነፃ ለመልቀቅ ይችላል ።
4. ዓ/ህግ ቅጣቱ አንሶል ብሎ ቅጣቱ ላይ ብቻ ይግባኝ ሲጠይቅ ቅጣቱን ያፀናል ወይም ይጨምራል ። ዓ/ህግ ብቻ ቅጣቱ ላይ ይግባኝ ጠይቆ ተከሳሹን ግን ይግባኝ ካልጠየቀ ቅጣቱን መቀነስ አይችልም።/
5. ተከሳሹ ቅጣቱ በዝቷል በማለት ቅጣቱ ላይ ብቻ ይግባኝ ከጠየቀ ቅጣቱን ያፀናል ወይም ይቀንሳል ። / ተከሳሽ ብቻ በቅጣቱ ላይ ይግባኝ ጠይቆ ዓ/ህግ ይግባኝ ካልጠየቀ ቅጣቱን መጨመር አይቻልም።

ክፍል ሶስት ፣ የሰበር ችሎት

1. የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል/ህገ መንግስት አንቀጽ 80/ሀ//።
2. የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዩች የተሰጠ የመጨረሻ ውሣኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል / ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ለ//።
3. ዝርዝር አፈፃፀሙን በተመለከተ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በአዋጅ ቁጥር 25/88 መሠረት የሚታይ ሲሆን የክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ደግሞ በክልሉ ህግ መሠረት ይታያል።
4. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የሰበር ችሎትን በተመለከተ / በአዋጅ ቁ. 25/88/፡-

   ሀ. የህግ ስህተት ያለባቸውን የሚከተሉትን ጉዳዩች በሰበር የማየት ስልጣን ይኖረዋል /ቁ. 10/።

   1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዩች ፣
   2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዩች፣

3. የክልል ጠ/ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት ወይም በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዩች ።።

ለ. የሰበር ክርክር የሚታየው ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየመበት ችሎት ነው /ቁ. 21/2/።።

ሐ. የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ስነ ስርዓት /ቁ. 22/፣

1. አንድ ውሣኔ በሰበር የሚሰማው አስቀድሞ ሶስት የጠቅላይ ፍ/ቤት ዳኞች የተሰየሙበት ችሎት ውሣኔው ለሰበር የሚያበቃ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ብሎ ሲወስን ነው ።።
2. ጉዳዩ በሰበር እንዲታይለት የሚፈልግ አቤቱታ አቅራቢ ጉዳዩ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚልበትን ምክንያት በማመልከቻው ላይ በዝርዝር ጽፎ ማቅረብ አለበት ።።
3. አቤት ባዩ ከማመልከቻው ጋር የይግባኝ የተባለበትን ውሣኔና የበታች ፍ/ቤት ውሣኔ ቅጂዎችን ማቅረብ አለበት ።።
4. የሰበር ጥያቄ ማመልከቻ ለፊደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት መቅረብ የሚገባው የሰበር ጥያቄ በሚቀርብበት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ በተሰጠ በዘጠና ቀን ውስጥ መሆን አለበት ።።

FRIEDRICH
EBERT
STIFTUNG

Friedrich- Ebert- stiftung is supporting the federal supreme court of the federal Democratic Republic of Ethiopia in publishing this bench book as one of the activites in its longstanding co- operation in the justice sector. The bench book should contribute to abetter transparency and efficiency of the justice system in Ethiopia like many other activities performed together in the past years as the support for the installation of touch screens, joint deliberations on the interpretion of the constitution or training programmes. The bench book may help judges to organize their court cases following the same rules and regulations in all parts of the country. This will help the citizens of Ethiopia to Know the federal law is the same and equal in all parts of the country and judgment is made according to the law. The bench book may help to minimize or to eradicate the disparities in the justice system between the regions in Ethipia and guarantee all citizens the same treatment by law.

Hartmut Hess
Resident Representative
Friedrich- Ebert- Stiftung
Ethiopia office

Published by Friedrich- Ebert- Stuftung. Ethiopia office, in co-operation with the court Administration Reform project and the Federal supreme court of the Addis Ababa, January 2006